



በሕዝብ መዋጮ በዚህ ዓይነት ፕላን ሊሠራ የታቀደው የደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያንን እርዱ



# ትንሣኤ

እንኳን ለዘመነ ማርቆስ አደረሰዎ




፲፱፻፸ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

21/04/1971

# ደብዳቤዎች

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
አዲስ አበባ

"ትንሣኤ" የተሰኘ መጽሔት በየጊዜው እያሳተማችሁ ለምዕመናን በተወሰነ ዋጋ እንደምታቀርቡ ግልጽ ነበር እስከ ዛሬ ሳይታተም የቀረው በምን ምክንያት ነው?

መርሐ ጽድቅ ዮሐንስ
ከአዲስ አበባ

—መጽሔታችንን ተከታትለው ለምን ሳይታተም ቀየ ማለትዎ በጣም የሚያስመሰግን ነው ፤

መጽሔቱ የሚታተመው በየጊዜው ሳይሆን በአንዳንድ በዓላት ምክንያት ነው ለብዙ ጊዜ የዘገየው ያሉት መጽሔቶች የታተሙበትን ዋጋ ባያወጡ እንኳን ከመጋዘኑ ቀለል እስከሚሉ ድረስ ነው ዛሬ ግን ደስ ይበለዎ ደስ ይበለን በየሁለቱ ወራት አንድ ጊዜ ለማውጣት ወስነን መጽሔቱን አሳትመናል ።

****

ድርጅታችሁ ስንት የሥራ ዘርፎች አሉት? ያሉትን ዘርዝራችሁ አስረዱኝ ።

ከአዲስ አበባ
አስናቀች ተገኝ

—ባጭሩ ለመጥቀስ
1ኛ/ የሥነ ጽሑፍ
ሀ/ ጋዜጣ
ለ/ መጽሔት ሌላም መጻሕፍት እያጠና የሚያሳትም ነው ።
2ኛ/ ሥነ ምግባር ተዘዋዋሪ ጓድ
ሀ/ በበዓላት
ለ/ በእሑድ ት/ቤት
ሐ/በአስፈላጊ ቦታዎችእያጠና ያስተምራል
3ኛ/ የቴፕ ሐዋርያ
ሀ/ መንፈሳዊ መልዕክት
ለ/ ጥንታውያንና ዘመናውያን መንፈሳውያን መዝሙሮች እየቀረፀ ለቅርስ የሚያስቀምጥና ለሚፈልጉ እንደአስፈላጊነቱ እያጠና የሚሰጥ ነው ይህኑም በነሐሴ ወር በወጣው ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ለመረዳት ይቻላል
4ኛ/ የማከፋፈያ ክፍል
ይህ ክፍል ከላይ የተጠቀሱትን የሥራ ዝርዝር እያጠና ለምዕመናን የሚደርሱበትን መንገድ የሚቀይስና የሚያደርስ ነው ።
5ኛ/ ትምህርት ቤቶች
ሀ በመናገሻ አውራጃ በሆለታ ወረዳ በርፈታ ከ1-6
ለ በጉጃም ክፍለ ሀገር በመተከል አውራጃ ቡለን በሚባለው ቀበሌ ከ1-6 ክፍሎች ያላቸው ብዙ ተማሪዎችን ያፈሩ ት/ቤቶች አሉን እንግዲህ የተሠማራነው በዚህ ዓይነት ሥራ ነው ለወደፊቱ ደግሞ ሥራችን እያስፋፋን ስንሔድ ለመግለጽ እንሞክራለን አንቺም ለመጠየቅ እንዳትሠለቺ ።

****

በየጊዜው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ይወጣል እየተባለ ይወራል መቼ ነው ወጥቶ የምንጠቀምበት?

ከማኅበረ ክርስቶስ መንፈሳውያን ወጣቶች ክፍል

—እኛም ሙት ዓመቱን አውጥተን ሁለተኛ ዓመቱን ጀምረናል የሚመለከተውን ስንጠይቅ የሚሰጠው መልስ ይወጣል ነው እንግዲህ እኛም እናንተም በናፍቆት መጠባበቅ ነው ።

እናንተ ታዘምሯቸው የነበሩት መንፈሳውያን የአማርኛ መዝሙሮች በምን ዓይነት ሊደርሱኝ ይችላሉ?

ተማሪ ገነት አበበ
ከአዲስ አበባ


—አንቺ የምትፈልጊው ዜማቸውን ነው ወይስ ግጥማቸውን ለሁሉም የሚደርሱበትን መንገድ እንድንገልጽልሽ አሳብሽን ተንትነሽ ጻፊልን ወይም በመጽሔቱ ላይ ያለውን የስልክ ቁጥር ተመልክተሽ ደውይልን ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በሁለት ወራት አንድ ጊዜ የሚታተም መንፈሳዊ መጽሔት ፦

የስልክ ቁጥር 116616
የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

## ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ፪ኛ/ የ፲፱፻፸ ዓ.ም. አጽዋማትና በዓላት | ፪ |
| ፫ኛ/ በአዲስ ዓመት አዲስ ሥራ | ፫ - ፬ |
| ፬ኛ/ ቤተ ክርስቲያን የማንናት ? | ከ፭-፮ |
| ፭ኛ/ ነገ ያንተ ናት | ፮ - ፯ |
| ፮ኛ/ ዜና አብያተ ክርስቲያናት | ፯ - ፱ |
| ፯ኛ/ ት/ ዘጉባኤ ማ/ቤት ያተማቸው አ/ መጻሕፍት | ፱ |
| ፰ኛ/ ሴቶች በሃይማኖት | ፲ - ፲፩ |
| ፱ኛ/ የመጽሐፍ ቅ/ማኅበር | ፲፩ - ፲፪ |
| ፲ኛ/ ታውቃላችሁን ? | ፲፪ |
| ፲፩ኛ/ ቤተ ክርስቲያንና እኩልነት | ፲፫ - ፲፬ |
| ፲፪ኛ/ የኢ/ተ/ቤ/ክ/ የልማት ኮሚሽን ለምን ተቋቋመ ? | ፲፭ - ፲፯ |
| ፲፫ኛ/ ልዩ ማሳሰቢያ | ፲፯ |
| ፲፬ኛ/ ቤተ ክርስቲያንና አላማዋ | ፯ - ፲፱ |
| ፲፭ኛ/ የምእመናን ድምጽ | ፲፱ - ፳፫ |




የሙካሽ ሥራ

## የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ካቴድራል ጽ/ቤት ከሚያካሂዳቸው የሥራ ዘርፎች

በእነዚህም ሆነ ወደፊት በምናስተዋውቃችሁ ዝግጅቶች ለመጠቀም የምትሹ ለማንኛውም ብትችሉ ወደካቴድራሉ ሱቆች ሄዳችሁ ለመረዳት ሞክሩ ።

ባትችሉ በስልክ ቁጥር 120170
በፖ. ሣ. ቁ. 3137 አዲስ አበባ ብላችሁ ጠይቁ



የሥጋጃ ሥራ



www.ethiopianorthodox.org

# የ፲፱፻፹ ዓ.ም. አጽዋማትና በዓላት

| በዓላት | አጿማት |
|---|---|
| አበቅቴ22 | |
| መስከረም 1 ቀን የዘመን መለወጫና ኤርትራ ከእናት ሃገሯ የተዋሃደችበት | መጥቅዕ 8 |
| መስከረም 2 ቀን የአብዮት በዓል | ወንጌላዊ ማርቆስ |
| ” 10 ተቀጸል ጽጌ (የቤተ ክርስቲያን በዓል) | ጾመ ነነዌ የካቲት 13 |
| መስከረም 17 መስቀል | ዓቢይ ጾም የካቲት 27 |
| ታኅሣሥ 29 ልደት | ደብረ ዘይት መጋቢት 24 |
| ጥር 11 ጥምቀት | ሆሣዕና ሚያዝያ 15 |
| ጥር 12 ቃና ዘገሊላ (የቤተ ክርስቲያን በዓል) | ስቅለት ሚያዝያ 20 |
| የካቲት 12 የኢትዮጵያ ሰማዕታት መታሰቢያ በዓል | ትንሣኤ ሚያዝያ 22 |
| የካቲት 23 የዓድዋ ድል መታሰቢያ | ርክበ ካህናት ግንቦት 16 |
| መጋቢት 28 የነፃነት በዓል | ዕርገት ሰኔ 1 |
| ሚያዝያ 23 የሠራተኞች በዓል | ጰራቅሊጦስ ሰኔ 11 |
| | ጾመ ሐዋርያት ሰኔ 12 |



# በአዲስ ዓመት አዲስ ሥራ

በሀገራችን በኢትዮጵያ መስከረም የዘመን መለወጫ ፣ የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነው ። ግን የመስከረም ወር የዘመን መለወጫ እንዲሆን ያደረጉት አባቶች ጥቅም አግኝተውበት ይሆናል ።

በአውሮፓውያን ደግሞ የጥር ወር የዘመን መለወጫ የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነው ። ይህም በቂ ምክንያት ያለው ይመስለናል ። ይኸውም አሮጌው የኦሪት ዘመን አልፎ አዲሱ የደኅንነት ዘመን የተተካበት ፣ ኦሪት ተሽሮ ወንጌል የተሾመበት ፣ ክርስቶስ ተወልዶ ሁሉን ነገር ያደሰበት በመሆኑ መልካም የዘመን መለወጫ ወር ነው ። ከዚህም ሌላ እስራኤላውያን የዘመን መለወጫቸውና የአዲስ ዓመት መጀመሪያቸው የሚያዝያ ወር እንዲሆን እግዚአብሔር በሙሴ ነግሮአቸው በታላቅ መንፈሳዊ ድምቀት ሲያከብሩት ኖረዋል ። ይህ እሥራኤል ያከብሩት የነበረው የዘመን መለወጫ በዓል ታሪኩ እንደሚነግረን በእርግጥ የዘመን መለወጫ በዓል ሆኖ ሊከበር የተገባው ነበር ለማለት ያስደፍራል ። ምክንያቱም እሥራኤል ከግብፅ ባርነትና ከጭቆና አገዛዝ ነፃ የወጡት በዚሁ በሚያዝያ ወር ስለሆነ አከባበሩ በቂ ምክንያት ስለነበረው ነው ።

ይህንኑ የሚያዝያን ወር የሚያከብሩት የቀድሞ ባርነታቸውንና በግብፃውያንም የተፈጸመባቸውን የዕብሪት አገዛዝ ርኅራኄ የጐደለውን የግብፅ ፈርኦኖችን አስተዳደር እያስታወሱ ፣ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ርኅራኄና ያጐናጸፋቸውንም ነፃነት ለልጅ ልጆቻቸው እያስተማሩ ነበር ።

አዎ በኢትዮጵያችንም ከፈርዖኖች ያላነሰ የግፍ አገዛዝ ፣ ከግብፃውያንም ያላነሰ ጨቋኝነት በጠቅላላው ለልጅ ልጆቻችን ልናስጠናው የሚገባ አንገፍጋፊ የባርነት አገዛዝ ተወግዶ ፍጹም ነፃነት ፣ ሰብአዊ እኩልነት የተገኘው በተለያዩ ወሮች ነው ። እነዚህ ወሮች ሁለት ናቸው አንደኛው የካቲት ፷፮ ሁለተኛው መስከረም ፷፯ ናቸው ። ታዲያ መስከረም የሚፈለግበትን ለውጥ ባያስገኝ ኖሮ በየካቲት ተለውጦ የዘመን መለወጫችን የካቲት በሆነ ነበር ። ዳሩ ግን መስከረም የካቲት የጀመረውን በማጠቃለል የበለጠ ቁም ነገር ሠርቶአልና መስከረም የዘመን መለወጫነቱን እንደያዘ ሕያው ሆኖ ይኖራል ።

በኢትዮጵያ ለብዙዎቻችን ትርጉሙ ሳይገባን እናከብረው የነበረው የመስከረም ወር የዘመን መለወጫ ከሁለት ዓመታት ወዲህ የምናከብርበት ግልፅ ምስጢር ስለያዘልን በመስከረም የተወገደልንን እብሪታዊ አገዛዝ ለልጅ ልጆቻችን ልናስጠናው የሚገባን ታሪክ ትቶልናል ።

ይኸውም ይህ የመስከረም ወር ከወራት ሁሉ ተአምር የተደረገበት ፣ የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠበት ፣ ፍጡር ከማምለክ የዳንበት ነፃነት የተገኘበት ፣ የምሥራችም የታወጀበት ፣ ትዕቢተኞች ከልዕልናቸው ዝቅ ዝቅ ያሉበት ጭቁኖች ኃይልን የተጐናጸፉበት ፣ ተስፋ ቆርጠው ከምድረ ኢትዮጵያ የተሰደዱ ሁሉ ወደምድረ ርስት የተመለሱበት መስከረም ነው ። እንግዲያውስ የመስከረም ወር በእርግጥም “አበባዬ መስከረም ጠባዬ” ተብሎ ሊዘመርለት የሚገባ የምስራች የተነገረበት አዲስ ወር ነው ።

እሥራኤል የሚያዝያን ወር በታላቅ ድምቀት ያከብሩት የነበረው ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ወር መጀመሪያ በባህረ ኤርትራ ግብፃውያን ጠላቶቻቸው ስለወደሙላቸውና በዚህም ወር ከጠላቶቻቸው አሳድጅነት ስለአረፉ ነው ። ከዚህም ጋር እሥራኤል ከሰማይ መና ስለወረደላቸው ለብዙ ጊዜ አርፈው ተቀምጠው ሲመገቡ ኖረዋል ።

የእኛው የዘመን መለወጫ መስከረም ግን የዕረፍት ሳይሆን አዲስ ሥራ በአዲስ መንፈስ ፣ በአዲስ ጉልበት ፣ ይፈልግብናል። በዚሁ አንፃር ከባርነት ወደ ነፃነት የተሸጋገርንበት አዲሱም ለውጥ ከእኛ አዳዲስና ተለዋጭ ሥራዎችን ይጠብቃል እንጂ ከሰማይ መናን ሊያወርድልን አልተዘጋጀም ።

ዛሬ ኢትዮጵያ ከፈርዖኖች እብሪት አልተገላገለችም ፤ በፈርዖኖች ዕብሪት የተወጠሩ የፈርዖኖች የሐሳብ ዲቃሎች የሆኑ አድሃሪ አረቦች ሊያስጨንቋት ይፈልጋሉ ። ታዲያ ዛሬ አድሃሪ አረቦችን እንደቀድሞዎቹ ፈርዖኖች በተአምር ኤርትራ ታስጥማቸው ብለን የምንጠብቅበት ጊዜ ሳይሆን ለእነርሱ መቅሰፍት የምንሆነው እኛው ራሳችን መሆናችንን መዘንጋት የለብንም ።

በባህረ ኤርትራ ሁለተኛውን ተአምር ሠርተን የጠላቶቻችን ስጥመት ለዓለም የምናሳውቀውም እኛው ስለሆን ለዚህ ታሪካዊ ድል በአዲስ ዓመት በአዲስ ጉልበት መዘጋጀት አለብን ።

በቀይ ባህር ተአምር እንዲሠራልን የሙሴን ክንድ ወይም የመናፍስትን ኃይል አንጠብቅም ። በቀይ ባህር ተአምር ሠርቶ ጠላቶቻችንን የሚያስጥማቸው የእኛ የተባበረ ክንድ ነው ።

ስለዚህም ዛሬ መስከረምን የምንቀበለው እንደቀድሞው በልዩ ልዩ ጌጣጌጥ አሸብርቀን አይደለም ጉልበታችንን አጠንክረን ኃይላችንን አስተባብረን የሥራ ልብሳችንን ለብሰን ለሥራ ታጥቀን መሆን አለበት ።

እንግዲህ አዲስ ሥራ የተጀመረበት ወር አዲስ ወር ነው ። ለውጥ የታየበትም ወር የዓመት መጀመሪያ ነው ። አዲስ ሥራ የሠራና ለውጥን ያሳየ ትውልድም አዲስ ትውልድ አዲስ ምዕራፍ ከፋች አዲስ ታሪክ መሥራች ተብሎ ሊታወስ የሚገባ ፣ ታሪኩም በሕያው ምዕራፍ ሊመዘገብ የሚገባ ሲሆን ታሪኩም በትውልደ ትውልድ ሲነበብ ይኖራል ።

ያለፉት አባቶቻችን ታላላቅ ሥራ ስለሠሩ ድንበራቸው



www.ethiopianorthodox.org

ንም ስለአስከበሩ የጊዜ ብዛት ሳያስረሳቸው ደመናውም ሳይ ሠውራቸው ፣ የታሪክ ሰዎች በመሆን በመላው ሕይወታቸው ትውልድን ሲያኮሩ ፣ ሲያስተምሩ ፣ ይኖራሉ ። ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ለመዋጥ ያቀዱት ዛሬ ብቻ አይደለም ። ታሪክ እንደሚያስተምረን ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ጥረት አድርገው ነበር ። ግን በአባቶቻችን ቆራጥነትና ጀግንነት በ እግዚአብሔር ረዳትነት እስከዘለዓለሙ ታሪክ የማይረሳው ትምህርት እየተማሩ የእሞራ ሲሳይ ሆነው ቀርተዋል ።

እኛም ዛሬ የአባቶቻችንን እምነት ፣ የአባቶቻችን አገር ወዳድነት አንስተን ታሪክ የማይረሳው ትምህርት ለማስተ ማር በዚህ አዲስ ዘመን መዘጋጀት አለብን ።

ለውጥን ለውጥነቱ እንዲታወቅ ለማድረግ እኛ መለ ወጥ አለብን ። በዓለም ዙሪያ ብዙ ለውጦች ተደርገዋል ። ግን የለውጥ ትርጉም በሥራ ላይ የዋለበት ጊዜ እጅግ በጣም ጥቂት ነው ። የለውጥ እንቅፋቱ ብዙ ነው ። በለውጡ ተጠ ቃሚ የሆነው ወገን ሳይቀር ባለማወቅ ለውጥን ሊያደናቅፍ ይሞክራል ። በዓለም ዙሪያ የሚደረጉት ለውጦች የዓለምን አንድነት አስተባብረው ታይተው አይታወቅም ።

ምክንያቱም እንቅፋት ስለሚገጥማቸው በእንጭጭነታ ቸውም እየተቀጠፉ ስለሚቀሩ ነው ። የእኛው ለውጥም እን ዲህ ዓይነቱ ቀጣፊ ተባይ እንዳይደርስበት ማድረግ የምንች ለው በተአምር አይደለም ። በሥራና በተባባሪ ክንድ ነው ።

ለውጥን ለመንከባከብ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ የመንፈስ ለውጥ ያስፈልጋል ።

የመንፈስ ለውጥ ከሌለ ግን ለውጥ ሊሰምር አይችልም፡ የተፈጥሮ ሥነ ሥርዓት የተወሰነለትን የለውጥ ጊዜ ሳያዛንፍ ለውጥን በሥራ ሲተረጉም እናያለን ።

እነሆ በአሁኑ ወር ሥነ ፍጥረት በሙሉ ታድሳ አዲሱን ዘመን ለመቀበል ተዘጋጅታለች ። እኛም ዛሬ የሚፈለግብን እንዲህ ዓይነት ለውጥ ነው ።

ስለዚህ የሚለዋወጥ ዘመን ካልሠሩበት ዋጋ የለውምና የለውጥን ትርጉም በሥራ ለማሳየት ከምንጊዜውም የበለጠ በዚህ አዲስ ዘመን መዘጋጀት አለብን ።

ከተስፋ ጥሩነህ



# ቤተ ክርስቲያን የማን ናት ?

አንድ ባላ አእምሮ ሰው የራሱን ቤት "ይህ ቤት የማን ነው ?" ብሎ ሊጠይቅ አይችልም ይሆናል ። ቢጠይቅ ግን ለሰ ሚው ግራ ሲሆን የሚችለው የጥያቄው መልስ ሳይሆን የሰውዬው አጠያየቅ እንደሚሆን ግልጽ ነው ። ምክንያቱም ባለቤቱ እንዴት የራሱን ቤት እንዳላ ወቀ ወይም ካወቀ ለምን እንደ ጠየቀ ፣ እንዲሁም አንድ ክርስቲያን "ቤተክር ስቲያን የማን ናት ?" ብሎ ቢጠይቅ የሚከብደው መልሱ አይደለም ። የጥያ ቄው መነሻ ምክንያት ነው ።

ይህ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንፃር ሲታይ በመሠረቱ የወል የነበረ ቤተ ክርስቲያን ከዘመናት በኋላ በልዩ ልዩ አህጉር በጥቂቶች ሰዎች የእኔ ባይ ነት እንደ ግል ቤት መቆጠር በጀመረበ ት ወይም ደግሞ አሳቢዎቹ ብዙዎች የእኔ ባዮቹ ግን ጥቂቶች እየሆኑ በሄዱ በነበረበት ዘመን በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ባዕድነትና እንግ ድነት የተሰማቸው ብዙኃን ካህና ትና ምእመናን ያቀርቡት የነበረውን የ ሕሊና ጥያቄ ያሳስባል ።

ቤተ ክርስቲያን የማን ነበረች ? የማ ን ናት ? የማን መሆን አለባት ? የሚለ ውን ጥያቄ መነሻ በማድረግ ወደ እውነ ተኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንገባ መልሱን በአጭሩ ማግኘት ይቻላል ። የእምነት ልዩነት መኖሩ ባይካድም የሰ ው ልጅ ያለ እምነትና ተስፋ መኖር የማ ይችል ልዩ ፍጡር እንደ መሆኑ መጠን ያለ አንዳች እምነት የኖረበት ጊዜና ቦታ አልነበረም ፣ የለም ፣ አይኖርም ። ይኸውም እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜና ቦታ በልዩ ልዩ መንገድ የመታ መንና የመመለክ ኃይል ያለው ከሃሊ አምላክ በመሆኑ ነው ። የቃለ እግዚ አብሔር መዝገብ የሆነው ቅዱስ መጽሐ ፍ "በፈጣሪ ፈንታ ፣ የተፈጠረውን አ መለኩ" ሲል (ሮሜ 1 ፣ 25) እንደተና ገረው ሁሉ አንዱ ክፍል ፈጣሪን በሥነ ፍጥረቱና በአስደናቂ ሥራው እንዲሁ ም በተነገረው ቃሉ የሚያውቅ ሃይማኖ ተኛ ሲሆን ሌላው ደግሞ ግዙፍ ሥራ ውን ብቻ የሚመራመርና የሚያምን ግማሽ አማኒ ይሆናል ። የሌላውን በዚ ሁ እናብቃና በተለይ በሙሉ አማንያን በኩል ያለውን የታሪክ ቅደም ተከተል ስንመለከት አምልኮተ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ደረጃ መካሄድ ከመ ጀመሩ በፊት በዘመነ አሪትም ሆነ ከዚ ያ አስቀድሞ በሕግ ጠባዕያዊና ሕግ መጽሐፋዊ መመሪያ መሠረት ሲፈ ጸም መቆየቱን የሃይማኖት ታሪክ ያስረ ዳል ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ቤተ ክር ስቲያን ስትመሠረት ግን ለክርስትና ዓለም ብቻ ሳይሆን ሌላውም ሁሉ ከፍ ተኛ ምሳሌነት ያለው ከተፈጥሮ በኋላ በተፈጠረ ሰብአዊ ተንኮል የተሰወረው የአንድነትና እኩልነት ፣ የነፃነትና ፍትሕ የእውነተኛ ፍቅርና ወንድማማ ችነት ኑሮ ምሥጢር በይፋ የሚገለጽበ ትና የሚሰበክበት አንደኛ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ማኅበር በዓለም ላይ ተ ፈጠረ ።

የዚህ ማኅበር አባል የሆኑ ክርስቲያ ኖች ሁሉ እንደ ማንኛውም ሰው በዓ ለም ላይ የግል ቤት ንብረት ነበራቸው፣ አላቸው ። ሁኖም የቤተ ክርስቲያን መ ሥራች የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ክርስቶስ "በስሜ ሁለት ሦስት ሁናች ሁ በተሰበሰባችሁበት በዚያ እኔ በመካ ከላችሁ እገኛለሁ (ማቴ ም. ፲፰ ቁ ፳) ሲል ስለ ኅብረት አስፈላጊነት በተናገረ ው መሪ ቃል መሠረት ክርስቲያኖ ች ለመንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊ ኑሮዋቸው የሚያስፈልገውን ግዳጅ በ ተናጠል ሳይሆን በኅብረት ለመፈጸም የማኅበር ቤት እንደሚያስፈልጋቸው ተ ረዱ ። በማኅበር መጸለይም ሆነ በማኅ በር መኖር የሚያስገኘውን መንፈሳዊና ሥጋዊ በረከት ከተረዱ በኋላ የቤተ ክ ርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ክር ስቲያኖች በየቦታው የማኅበር ቦታ በኅ ብረት መሥራት ጀመሩ ። ያም የማኅ በር ቤት አሁን "ቤተ ክርስቲያን" እያ ልን የምንጠራው ቤተ ጸሎት ነው ። ይህ የጸሎት ቤት በሌላ አነጋገር "ቤተ እግዚአብሔር" እየተባለ ይ ጠራል ። ይኸው አንዱ ቤተ ጸሎ ት ቤተ ክርስቲያንና ቤተ እግዚአብ ሔር እየተባለ የሚጠራውም በእምነ ትና ጸሎት አማካይነት ሰውና እግዚአ ብሔር የሚገናኙበት በእርግጥ የማኅ በር ቤት መሆኑን ለማመልከት ነው ። አስፈላጊነቱ ታውቆ በክርስትና ዓለም ላይ የማኅበር ቤት ወይም ቤተ ክርስቲ ያን በሰፊው እንዲኖር ከተደረገ ወዲ ህም ቤቱ የማኅበር እንደመሆኑ መጠን ኃላፊነቱም የጋራ መሆን እንዳለበት ስለታመነበት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለ ማንም ግለሰብእ የእኔ ባይነት ቤተ ክር ስቲያን የሕዝበ ክርስቲያን ሁና በዘኅ ብረት ስትተዳደር ኑራለች ።

ሁኖም ይህ የታሪክ ፈለግ በዚሁ አቅ ጣጫ እስከ መጨረሻው ወደ ፊት ለመ ጓዝ ያልቻለበት ጊዜና ቦታ መኖሩ አይ ካድም ። ይኸውም ከዘመናት በኋላ በአ ንዳንድ አህጉር የባላይነትና የትክለኛ ሥሪት በመጀመሩ ነው ። ከእነዚህም አህጉር አንዷዋ ኢትዮጵያ ናት ። ነገር ግን የማኅበር የነበረችውን ቤተ ክርስ ቲያን እንደገና በግለሰብእ ደረጃ መከፋ ፈሉ የቤተ ክርስቲያን መሠረት አቋም ማናጋት ከመሆኑም በላይ ለቤተ ክርስቲ ያን ዘላቂ ሕልውና ዋስትና የሌለው አሠራር መሆኑ በግብር እየሆነ እየተረ ጋገጠ ስለሄደ ዛሬ በምሥራቃዊውም ሆነ በምዕራባዊው የክርስትና ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንደገና የሕዝበ ክር ስቲያን ሁናለች ። ሕዝበ ክርስቲያ ኑ ለማኅበር ቤቱ በማኅበር ማሰብና ለሚያስፈልገውም የወር ወጭ ያለ ጭቅጭቅና ንዝንዝ የተባበረ እ ጁን መዘርጋት የተለመደ የክርስትና ሕይወት መመሪያው ከሆነ ቆይቷል ። እንዲያውም በአንዳንድ ሀገር አንድ ክ ርስቲያን ባለቤት ለምሳሌ ሁለት ቤተ ሰብእ ቢኖረው ቤተ ክርስቲያንን እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ሦስተኛ አራት ያለውም እንደ አምስተኛ ቤተ ሰብእ በመቆጠር በፈቃዱ የወር ወጭ ከሚመድብበት ደረጃ መድረሱን የጊዜው ታሪክ ያረጋግጣል ።

ይህንም ለማድረግ የሚገደደው ቤተ ክርስቲያን ራስዋን የቻለች ድርጅት እንደ መሆኗ መጠን አንድ ድርጅት ስለ ሠራተኛ ፣ ሠራተኛም ያለ ልብስና ጉርስ መኖር የማይችል መሆኑ ከታወቀ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ኑሮ ለመጠበቅ የማሠልጠኛ ት/ቤቶችን የማይቋረጥ ተግባር ለማካሄድና በጠቅላላ ትምህርት ሃይማኖትን ለማጠናከር የሚያገለግሉ ጽሑፎችን ለማዘጋጀት የገንዘብ ኃይል እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ ነው ።

የሌላውን በዚሁ አሳጥረን የታሪክ ገጾችን ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንመልስ ደግሞ የምንመለከተው ቤተ ክርስቲያንን የሕዝበ ክርስቲያን ለማድረግና ራሷን ለማስቻል የሚደረገው ጉዞ በብዙ ርቀት ወደ ኋላ የቀረና እርምጃውም አብዛኛውን ጊዜ ከግብር ይልቅ የጎሲና መሆኑን ነው ። በመሠረቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ በሕዝበ ክርስቲያኑ የጎብረት ድጋፍ ብቻ የቆመች እንደ ነበረች የማይታበል ሐቅ ነው።ለዚህም ያለን አጭር ማስረጃ እስከ አሁን ከካህናቱና ምእመናን አእምሮ ያልጠፋው የአሥራት በኩራት ትዝታ ነው ። ሆኖም ቤተ ክርስቲያኒቱ ከመንግሥት ጋር በነበራት ቅርብ ግንኙነት ምክንያት ያን ጊዜ መንግሥት በመሬት ይዞታ ላይ አዲስ ሥሪት ሲተክል የቤተ ክርስቲያንም አቋም በዚያው አንፃር እየተለወጠ ሄደ በየቦታው በሕዝብ ትብብር የተተከሉትም ሆነ አዲስ የሚተከሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በጥቂቶች ግለሰቦች ባላባትነትና ትክለኛነት እንዲያዙ ተደረገ ። ይህ በመሆኑም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በማኅበረ ክርስቲያኑ መካከል "ባላባትና ትክለኛ መጤና ቶፋ" የሚል አደገኛ የሆነ ልዩነት ተፈጠረ ፣ የእኛ የእኛ ማለት ቀርቶ የእኔ ማለት ተጀመረ ። ያን ጊዜ በቀላሉ የተጀመረው ይህ ዓይነቱ ልዩነትም አደገኛ የሆነ ልማድን በማስከተሉ በአሁኑ ጊዜ ከኃላፊነት የራቀውን ሕዝብ አቅርቦ እንደገና ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ከባድና አድካሚ ሊያደርገው ችሏል ።

በጊዜው የነበሩት አባቶቻችን ይህን መንገድ የተከተሉት በእርግጥ ለግል ጥቅም ሳይሆን ከእምነታቸው ጽናት የተነሣ እነሱ ኃላፊዎች መሆናቸውን በማሰብ የሚወዷትን ቤተ ክርስቲያን በማያልፍ ርስት ላይ ለመትከልና ያለችግር ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመሸጋገር እንድትችል ለማድረግ በማሰብ እንደነበር መደበቅ አይቻልም ። ሁኖም የቤተ ክርስቲያን ርስት ጉልት መሬት ሳይሆን እምነት ብቻ መሆኑን አባቶቻችን ተገንዝበውት ቢሆን ኑሮ የሚወዷትን ቤተ ክርስቲያናቸውን ከችግር ላይ ላለመጣል ያን የነበረውን ትክክለኛ አሠራር በዚህ ዓይነቱ ባለወጡትም ነበር ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በእምነት ላይ እንጅ በርስት ላይ ካለመሆኑ በላይ በጋሻ መሬትና የመስቀል መሬት ሥሪት ሕዝበ ክርስቲያኑን ከፋፍሎ የመቅደስ መሬት ይዞታ ያለው ክርስቲያን ብቻ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲያስብ እያስገደዱ ሌላው ክርስቲያን እጁን አጣምሮ እንዲመለከት ማድረግ የሚጐዳው ራስዋን ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ ነበር ። ደግሞም አማንያን ከሌሉ ቤተ ክርስቲያን እንደ ዛፍ ከመሬት ላይ ተተክላ ልትበቅል አትችልም ።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ በማቋቋም ቤተ ክርስቲያንን እንደገና የሕዝብ ለማድረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ ትክክለኛና አስፈላጊም ስለሆነ የቅስቀሳውና የማደራጀቱ ተግባር በሰፊው መቀጠል ይኖርበታል ። በማንኛውም የኢትዮጵያ ምድር ላይ ያለ ማንኛውም ክርስቲያን ከተሜም ሆነ ገጠሬ ገበሬም ሆነ ነጋዴ ሁሉም እንደ ክርስቲያንነቱ ለሚገለገልባት ቤተ ክርስቲያን በባለቤትነት ደረጃ ማሰብ ይገባዋል ። ለማኅበር ቤቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ መተባበር ይኖርበታል ።

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስና ከኅብረተሰቡ የሚደርሱትን ሁሉ መልካም ጥሪ በመቀበል ሦስቱን የሰው ዘር ጣምራ ጠላቶች ለማውደም በሚደረገው ዘመቻ ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባት እነዚህም ድንቁርና ፣ በሽታና ረሃብ ናቸው ይህ ዓይነቱም ዘመቻ መጀመር ያለበት ከዚኸው ከደጅ ነው ። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን የማኅበር መሆኗን አምኖ የገንዘብ ኃይልን በማስተባበር የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑትን ካህናት 1ኛ/ በቂ ደመወዝ አግኝተው የተጐሳቆለ ኑሮዋቸው እንዲሻሻል ፣ 2ኛ/ የተማረውን ትውልድ ለማስተማር ይበቁ ዘንድ በኰሌጅና ሰሚናር ደረጃ እያሠለጠኑ ዕውቀታቸው ከፍ እንዲል ፣ 3ኛ/ በችግር ምክንያት የሚታወከው ጤንነታቸው በሚኖራቸው የዕውቀትና የገንዘብ ዓቅም እንዲጠበቅ ማድረግ ነው ። ምክንያቱም ራሳቸው ካህናትም ሆኑ ቤተ ሰቦቻቸው የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል በመሆናቸው ራሱ ክርስቶስም በዓለም ኅብረተ ሰብእ መካከል ይመላለስ በነበረበት ዘመን ይፈጽማቸው ከነበረው ዓበይት ተግባሮች አንዱ ድንቁርናን ፣ በሽታንና ረሃብን ማስወገድ እንደነበር በወንጌል ተጽፏል ። ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን በመጀመሪያ ሕዝበ ክርስቲያኑ በሰበካ ጉባኤ ተደራጅቶ ያለውን የሰውና የገንዘብ ኃይል ለማስተባበር ሲችል ነው ። ያለ ኅብረት ድርጅት ሊፈጠር አይችልም ፣ ያለ ድርጅት ደግሞ ለተባበረ ሥራ መሰለፍ አይቻልም ። ነገሩ የወይፈን እርሻ ይሆናል ። ስለዚህ ያሁኑ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ተግባር 1ኛ/ ቤተ ክርስቲያን የጥቂቶች ትክለኞችና በላባቶች ሳትሆን በእምነት የሁሉ መሆኗን ፣ 2ኛ በየጊዜው በግለ ሰብእ ደረጃ መስጠትም ሆነ መቀበል ለቤተ ክርስቲያን ችግር መፍትሔ ሊሰጥ እንደማይችል ባለፈው የተረጋገጠ ስለሆነ ሁሉም በሰበካ አስተዳደር ጉባዔ ተባብሮ የተባበረ እጁን በመዘርጋት የራሱን ቤተ ክርስቲ

ተከታዩን በገጽ ፱ ይመልከቱ



# ነገ ያንተ ናት

ቤተ ክርስቲያን ትናንት ነበረች ዛሬም አለች ። ነገም ትኖራለች ። በንግግር ዘይቤ ትናንት ስንል አንድ ቀንን ብቻ አያመለክትም ። በሽና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዘመናትን ያጠቃልላል ነገም ስንል የዛሬይቱ ጀንበር ገብታ የምትወጣበትን ቀን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ያለውን ዘመን ይጠቀልላል ።

እንግዲያውስ "ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ" እንዲሉ ቤተክርስቲያን ትናንት የማን ነበረች ዛሬስ የማን ናት ነገስ ? ወደሚለው ዝርዝር ጉዳይ መግባት ይኖርብናል ።

ብሔራዊት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ከተመሠረተች ጀምሮ ለሃገራችን የሰጠችውን አገልግሎት የመተንተን ድርሻ ለታሪክ ጸሐፊዎች እንተወውአለን ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቃለ መርሐእምነት አንድነት ፍቅርና ሰላም ነው ። ቤተክርስቲያናችን የጐሣ ፣ የብሔረሰብ ፣ የቋንቋና የፆታ ልዩነት ሳታደርግ መንፈሳዊ ትምህርት ስትሰጥ ኑራለች ። ለዚህም ከምፅዋ እስከ ሐመር ባኮ ከአሶሳ እስከ ጐዴ ያሉት አድባራትና ገዳማት ታቅፈውና ተደግፈው የሚኖሩት በተለያዩ ብሔረሰቦች በሚደረገው የበጐ ፈቃድ አስተዋጽአ በመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው።

በዚህ ምክንያት በኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መካከል ኅብረትና አንድነት ስለተፈጠረ የሃገራችን ዳር ድንበር ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ተጠብቆ ሕልውናዋ ታውቆ ኑሮአል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሃገር ላይ ለሚመጣው ጉዳይ ሃይማኖቱ አይፈቅድም ጦርነት አልሄድም የሚል ትርኪ ምንኪ አታውቅም ። በሃገር ቀልድ አለመኖሩን ጥርት አድርጋ ታውቃለች ። ሃገር ከሌለ ሃይማኖት የለምና ። ለዚህም እምቢ ለሃገሬ በማለት የፋሽስትን መንግሥት በማወገዝ ሰማዕትነት የተቀበሉትን አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ ሚካኤልን መጥቀስ ይበቃል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰላምን ታስተምራለች ፍቅርን ትሰብካለች ። በግፍ ለሚመጣውም ዋጋውን ትሰጣለች ። በዚህ መሠረት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉት ካህናት ከላይ መስቀል ከታች ሾተል ያለው የብረት ዘንግ ከእጃቸው አይለይም ። በሰላም የመጣውን በመስቀሉ ለመባረክ በጸብዕ የመጣውን በሾተሉ ለመዘትረክ ነው ።

ማኅበራዊ ጉዳይንና ልማትን የሚመለከቱ ነገሮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ድርሻ አበርክታለች ። እኛ አልተጠቀምንበትም እንጂ በአውሮፓናበአሜሪካ የሚገኙ ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች የኢትዮጵያን ብራና መጻሕፍትና ሥዕሎች በታላቅ ጥንቃቄ በመያዝና እንግዶችን በማስጐብኘት በብዙ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ ይለቅሙበታል ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ሃገር ጐብኝዎች አግበስብሰው የሚወስዱት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምታመርተውን መስቀልና ጌጣጌጥ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የራሷን ፊደል በራሷ ሊቃውንት አዘጋጅታ መጻሕፍትን በመተርጐምና በመድረስ የሥነ ጽሑፍ መዲና ሁና ኑራለች ። በዚህም ከፍተኛ ዝናን አግኝታበታለች ለምሳሌ በእብራይስጥና በዕርእ ቋንቋ ተጽፎ የነበረው ሄኖክ የሚባለው ትልቅ የሃይማኖት መጽሐፍ በዓለም ላይ ሲጠፋ በግዕዝ ተጽፎ ተገኝቷል ። አሁን ይህ መጽሐፍ ከኢትዮጵያ የተገኘ እየተባለ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመተርጐም ላይ ነው ።

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ዓላማ ብቻ አልተመሠረተችም የሰዎችንም ሥጋዊ ፍላጐት አብራ ተመልክታዋለች ። የሥጋዊ ፍላጐቶችን የሚያጠቃልለው የደን ሀብት ነው ። ደን ካለ ሥጋም ፍራፍሬም ከዚያው ይገኛል ። ይህን በመረዳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን አቅሟ በሚፈቅደው መሠረት ዕፀዋትን አስከብራ ኑራለች ። ለምሳሌም ያህል በመላ ኢትዮጵያ ያሉት አድባራትና ገዳማት በብዙ መቶ ዓመታት የሚቆጠሩ ዕድሜ ባላቸው ልዩ ልዩ ዛፎች ተከበው ይታያሉ ። እንደ ጽድ ዝግባ ኮሶ ፣ ወይራ ፣ ጥቁር እንጨት ዋርካ ሾላ ሰገድና የመሳሰሉት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ዛፎች የሚገኙት በቤተክርስቲያን ዙሪያ ነው ። የቀድሞው መንግሥት የቤተክርስቲያንን ፈለግ ተከትሎ ዕፀዋትን ቢንከባከብ ኑሮ ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት ሀገሮች ሁሉ በደን ሀብት የመጀመሪያዋና ምድረ ገነት ትሆን ነበር ።

በአጭሩ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነገሮች አከናውናለች ። እርግጥ በዘመናት መካከል በግለሰቦች ስግብግብነት ቤተክርስቲያን የነገሥታትና የመሳፍንት ግብር አበር ሁና መቆየቷ አይካድም ። አንድ አንድ የመሳፍንት አካል መንፈሳዊ መሪዎች የቤተክርስቲያንን ክብር ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ሸጠዋል ። ሰውን በማነፅ ፈንታ ድንጋይ ሲከቡ ሀብት ሲያካብቱ ኑረዋል። ይህ ምዕመናኑንና ብዙኃኑን ካህናት አይመለከትም

የገጠሪቱ ቤተክርስቲያን ሀብት ንብረቷ ምዕመናን ናቸው ። ምዕመናን ቤተክርስቲያናቸውን በጭቃ በጨፈቃ ሠርተው ዕጣንና ጧፍ ገዝተው ዘቢብና መገበሪያ አቅርበው ሲያስቀድሱባት ሲያስወድሱባት ኑረዋል ። ካህናቱም በሥራው ቀን እንደገበሬ በማረስ በበዓላት ቀን መቅደስ ገብተውበመቀደስ ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ኑረዋል። አሁንም ያገለግላሉ ።

የኢትዮጵያ ምዕመናን ሕይወት ከቤተክርስቲያን ጋር የተያያዘ ነው ሲወለ



www.ethiopianorthodox.org

ድ ይጠመቅባታል ለአቅመ አዳም ሲደርስ ይዳርባታል ። ሲታመም ይፈወስባታል ። ሲሞት ይቀበርባታል ።

በሰለጠነው ዓለም ያሉ ሰዎች ከፍተኛ የአእምሮ ጭንቀት አለባቸው ። ጭንቀቱን የሚያቃልሉ ሃኪሞች ተዘጋጅተዋል ። መድኃኒቱም በገፍ ይቀርባል የኢትዮጵያ ምዕመናን ግን የአስተዳደር በደል ተጭኖአቸው ስለኖረ እንኳን የአእምሮ ጭንቀት የሚያቃልሉ ሃኪሞች የተስቦ በሽታ መርፌ የሚወጉ ድሬሰሮች በቅርቡ አያገኙም ። ከበሽታው የሚድነው ጭንቁቱን የሚያቃልለው በጧት በማታ የሚሳለማትን ቤተክርስቲያን ጋሻ መከታ አድርጐ ጸበል በመጠጣት እምነት በመቀባት ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የምዕመናን መመኪያ መጠጊያና መጽናኛ ናት ። ምዕመናንም ስዕለታቸው ስለሚደርስላቸው ጸሎታቸው ስለሚሰማላቸው ጨለማውን ሳይፈሩ ብርዱን ሳይሸቆረሩ ወደ ቤተክር ኒያን ይጐርፋሉ ።

በሠለጠነው ዓለም ያሉት ሰዎች ከፍተኛ ጭንቀት የሚያጠቃቸው የብቸኝነት ኑሮ በመኖራቸው እንደሆነ ሲቃውንት ይናገራሉ ። እንዳንዱ ግለሰብ የሚኖረው እንደወንደላጤ ዝንጀሮ ከኅብረተሰብኡ ተለይቶ ነው ። ግፋ ቢል ማኅበራዊ ኑሮ የሚባለው ባልና ሚስት ከነ ልጆቻቸው አብረው ሲኖሩ ነው ወላጆች ወንድምና እኅት አጐትና አክስት አብሮ የመኖር ዕድል አይገጥማቸውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ግን ሰው ማኅበራዊ እንሰሳ ነው የሚለውን ፍልስፍና ተከትላ እንኳን ቤተሰብ ባዕዶች አብረው እንዲኖሩ አብረው እንዲበሉና እንዲጠጡ ታስተምራለች ። አቀራረቡ ይሻሻል ይባል እንደሁ እንጂ እንደ ሰንበቱ ፡ ጽዌ ፡ ክርስትናና ዝክር የመሳሰሉት ነገሮች ለማኅበራዊ ኑሮ እጅግ ተፈላጊዎች ናቸው ። ሌሎች ሃገሮች እነዚህ ነገሮች ስለጐደሉአቸው እኛ ስንፈጽማቸው ሲያዩ እንደ ብርቅና ድንቅ ያዩአቸዋል ። ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ምዕመናን ሕይወት ከቤተክርስቲያን ጋር የተሳሰረ ነው ያልነው ።

በእምነታችን መሠረት ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም ስለተመሠረተች ዘላለማዊት ትናንት የነበረችው ቤተክርስቲያን ነገም ትኖራለች ። ከላይ እንደተመለከትነው ለኅብረተሰብኡ የምትሰጠው አገልግሎትም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ይህ አገልግሎት ነገም መቀጠል ይኖርበታል ። ቤተክርስቲያን ፍርድ ጐደለ ድኃ ተበደለ ብላ የምትቆም ጠበቃ ናት ።

የነገይቱ ቤተክርስቲያን ሕልውና ዋስትና የሚኖራት ወጣቱ ትውልድ ተምሮ ለማስተማር ሲችል ነው ። ምዕመናን ልጆቻቸው ሐልወተ እግዚአብሔርን እንዲመረምሩ ቤተክርስቲያንን እንዲያዘወትሩ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው ። ካህናትም የነበራቸውን አስተሳሰብ ለውጠው ወጣቶቹ ወደ ቤተክርስቲያን የሚቀርቡበትን መንገድ መፈለግና ማስተማር ግዴታቸው ነው በተለይ ወጣቶች የነገዎቹ ተረካቢዎች ስለሆኑ በጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶች ሳይፈሩና ሳይሸበሩ የቤተ ክርስቲያናቸውን እምነትና ታሪክ ጠንቅቀው ማወቅና መረዳት ይኖርባቸዋል ። ነገ የነርሱ ናትና፤

ከሐዲስ ተረፈ

## ዜና አብያተ ክርስቲያናት

አስራ አምስት ሚሊዮን ተከታዮች ያሏት የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ርእሰሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ በመሆን በሩማንያ የሞልዶቪያ ክፍለ ሀገር ሜትሮፖሊስት ጁስቲን ሞይሲስኩ የተመረጡ መሆናቸውን ከቡካሬስት የተገለጠ መሆኑን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የማስታወቂያ ክፍል (ኤፒኤስ) ገለጠ ።

ምርጫው የተከናወነው ሰኔ 5 ቀን ሲሆን በምርጫውም ላይ የተካፈሉት በሩማንያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች ከምዕመናንና ከካህናት የተወከሉ የቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖችና እንዲሁም ከመንግሥት ሹማምንት የተውጣጡ መሆናቸው ታውቋል ።

✶✶✶✶

የስዊድን ቤተ ክርስቲያን በዘር ልዩነት ለሚሰቃዩት አፍሪካውያን ሁለት

<u>መቶ አምስት ሺ ብር ዕርዳታ አገኘ ።</u>

ዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በዘርና በቀለም ልዩነት በሚያካሒደው ግፍና በደል የተነሣ ለሚሠቃዩት አፍሪካውያን ዕርዳታ ይሆን ዘንድ የስዊድን ሉተራን ቤተ ክርስቲንን 205 ሺ ብር (ሁለት መቶ አምስት ሺህ የኢትዮጵያ ብር) ዕርዳታ የለገሠች መሆኗን አንድ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የዜና አገልግሎት ዕትም ባወጣው መግለጫ አስታወቀ ።

የስዊድን ሉተራን ቤተ ክርስቲያን ከአሁን ቀደምም ቢሆን ተመሳሳይ ዕርዳታ በመሰብሰብ 7006800 የኢትዮጵያ ብር ያህል የሰጠች መሆኑ ታውቋል ። የዓለም የብያተ ክርስቲያናት የዜና አገልግሎት ዕትም ጨምሮ በሰጠው መግለጫ መሠረት የርዳታው ገንዘብ የሚውለው በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሕጋዊ መብታቸውን አጥተው ቤተ ሰቦቻቸው ለታሰሩባቸው አፍሪካውያን መሆኑን አመልክቷል ።

✶✶✶✶

በ1850 አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ

<u>ጉባኤ መቋቋሙ ተገለጠ ።</u>

በጐጃምክፍለ ሀገር ከሚገኙት 2571 የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት በ1850 አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ የተቋቋመ መሆኑ ከጐጃም ሀ ስብከት ጽ ቤት በተላለፈው ዜና ተገለጠ በቀሩትም አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ የመቋቋሙ ሁኔታ በመጣደፍ ላይ መሆኑን በደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሏል ።

✶✶✶✶

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የዝቋላን ገዳም ወፍጮ በ $5008.25 አስጠገነ ።

ተከታዩን በገጽ ፱ ይመልከቱ



# ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ያተማቸው አዳዲስ መጻሕፍት

"ሃይማኖት አይለያየንም"
ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ሕይወት
፵፰ ገጽ
ዋጋው $1 አንድ ብር
አታሚ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት
ፖ. ሣ. ቁ. 31240
አዲስ አበባ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሃይማኖታቸው ምክንያት አንዱ ክፍል ሌላውን በጥርጣሬ ይመለከተው እንደነበረ ገልጸው ሁለቱን ሃይማኖቶች ከሚለያዩዋቸው ነጥቦች ይልቅ የሚያመሳስሏቸው እንደሚበልጡ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቁርዓን በመጥቀስ ያስረዳሉ ። እንዲሁም የሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች በአንድ አምላክ ስለሚያምኑ እምነታቸው ተመሳሳይ መሆኑን ይገልጻሉ ። ለዚህ መጽሐፋቸው መነሻ የሆናቸው በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል ከጥር ፳፱ እስከ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.በሊብያ ተደርጐ የነበረው ስብሰባ ነው ።

ይህ መጽሐፍ ወንድማማች የሆኑት የሁለቱም እምነት ተከታዮች መምህራን በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ከሚያለያዩዋቸው ነጥቦች ይልቅ የሚያመሳስሏቸውና የሚያቀራርቧቸው የሚበልጡ መሆኑን ስለሚረዱት ተከታዮቻቸው በይበልጥ እንዲቀራረቡና ወንድማማችነታቸውን እንዲያጠነክሩ በማስተማር መተባበርንወንድማማችነትንና ፍቅርን እንዲመሠርቱ እንዲያበረታቱዋቸው ይመክራል ።

### አዲስ መጽሐፍ

"አግብቼሻለሁ"
ከዋልተር ትሮቢሽ ተጽፎ
ከተስፋዬ ግርሻ ተተረጐመ
፻፹፯ ገጽ
ዋጋው $3 (ሶስት ብር)

ይህ መጽሐፍ የሚተርከው ስለ ጋብቻ ነው ። ደራሲው ዋልተር ትሮቢሽ በአንድ የቤተክርስቲያን ቄስ ጋባዥነት ከአውሮፓ ስሟ ወዳልተጠቀሰ አንድ የአፍሪካ ሀገር መጥተው በቤተክርስቲያን ውስጥ በብዙ መቶ ለሚቆጠሩና በተለያየ ዕድሜ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ንግግር በማድረግ ጋብቻን ለማጠናከር ምክር ይሰጣሉ ። ደራሲው ምክራቸውን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያደርጉት ንግግር ብቻ ሳይወስኑ አርፈውበት በነበረው ሆቴል ውስጥም በጋብቻቸው ችግር ለገጠማቸው ሰዎች ምክር በመስጠት ችግራቸውን ለማቃለል ምክር ይሰጣሉ ።

ዋልተር ትሮቢሽ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ገለጹት በጋብቻ ላይ ችግርን ከሚያመጡቅ ነገሮች መካከል በዕድሜ ፡ በትምህርትና በአስተሳሰብ ያለ መመሳሰል ፡ እንዲሁም ከጋብቻ በፊት በችኮላ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ይገኙበታል ።

ደራሲው በጋብቻ አማካሪነት የብዙ ጊዜ ልምድ ስላላቸው አንድ ሰው ከማግባቱ በፊትና ካገባም በኋላ ጋብቻው እንዳይፈርስ መደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይገልጻሉ ። ዛሬ በሀገራችን ውስጥ ካሉት ታላላቅ ችግሮች አንዱ ከቤተሰብ ልልነት የተነሣ በየጊዜው የብዙ ሰው ትዳር እየፈረሰ በመቅረቱ በየከተሞች የሴትኛ አዳሪነት ሥራ መስፋፋት ነው ። የቤተሰብ ልልነትም የሚመጣው ከጋብቻ ባፊትና በኋላ መደረግ የሚገባው ጥንቃቄ ሳይደረግ እየቀረ በመሆኑ ይህ መጽሐፍ ጋብቻን ለማጠናከር ለሚደረገው ጥረት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ስለታመነበት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለሕዝብ እንዲቀርብ ሆኗል ።

## ዜና አብያተ......

ከ፰ኛው ገጽ የዞረ

በዝቋላ ገዳም የሚገኙት መነኮሳትና ደካሞች ይተዳደሩ የነበሩት ቀደም ሲል ከመሬት በሚገኝ ጥቅምና አሁንም የገዳሙ ንብረት በሆነው በዚሁ የእህል ወፍጮ ኪራይና እንዲሁም ከምዕመናን በሚገኝ ዕርዳታ መሆኑን በተጨማሪ ከገዳሙ የተገኘው ዜና አስታውቋል ።

## ቤተ ክርስቲያን ......?

ከ፪ኛው ገጽ የዞረ

ያን ችግር በራሱ ማስወገድ እንዳለበት ማስረዳትና ማሳመን መሆን አለበት ።

ይህ ከሆነ ያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የሕዝበ ክርስቲያን ትሆናለች። ቤተ ክርስቲያን የማን ናት የሚለውም ጥያቄ ያን ጊዜ ትክክለኛ መልሱን ያገኛል ።

መልአከታቦር ተሾመ ዘርይሁን

## ችግረኞችን እንርዳ



የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ችግረኞችን እንድንረዳ እንዲህ ይላል ። ለችግረኞች ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል ምሳ 19 ፡ 17 ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው መዝ. 40 ፡ 1 በተድላው በደስታው ጊዜ ከእርሱ ጋር ደስ እንዲለው በተቸገረ ጊዜ ለባልንጀራህ አበድረው ሲራክ 29 ፡ 2 ምጽዋት ሁሉ ይቅርታን ያመጣል ሲራክ 16 ፡ 14



www.ethiopianorthodox.org

# ሴቶች በሃይማኖት

የሰው ልጅ በመጀመሪያ ደረጃ ተፈጥሮን ለመቋቋም ችሎታው በማይፈቅድለት ፥ ተፈጥሮን ለሱ የማዋል ጥበብን በሥራ ልምድ ባላገኘበት ዘመናት ፥ ኑሮን ለማሸነፍ ይችል ዘንድ በአንድነት በዘሕብረት መኖር ግዴታው ነበር ። በመሆኑም ግላዊ የሀብት ስሜት አልነበረም ። ስለሆነም የምርት መገልገያዎችና የምርት ማፍሪያ መሳሪያዎች በጠቅላላው በኅብረተሰብ ፤ የሚመረተው

በጠቅላላው ኅብረተሰብ ፥ ምርቱም የጠቅላላው ኅብረተሰብ ነበር ። የነበረውም የሥራ ክፍያ ተፈጥሮአዊ እንጂ እንደዛሬው በወንድ ትምክህተኝነት የተወጠረ ፥ የተቀየሰ ፤ የተበየነ አልነበረም ። በዚህ ኅብረተሰብ ደረጃ የነበረው የምጣኔ ሀብትም በማምረት ተግባር ውስጥ ከፍተኛውን ሚና የሚጫዎት ፥ ዋናውን የምርት ሥራ ለሚያከናውን የኅብረተሰብ ቡድን ወይም መደብ መፈጠር ከቶውንም መንገድ አይሰጥም ነበር ። አንዱ ሰው ለሌላው ሰው ጥገኛ የመሆን አጋጣሚ ስላልነበረ ፥ የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ፥ የኅብረተሰቡም ወሳኝ አካል የሆነችው ሴትም የኤኮኖሚ ጥገኛ አልነበረችም ። እንዲያውም ሰፍኖ በነበረው በዚህ ሥርዓተ ማኅበር የማምረት ሁኔታ ማለትም በጥንታዊው የእርሻ የማምረት ዘዴ ውስጥ ሴቶች ከፍተኛውን ሥፍራ ይዘው የማምረትን ተግባር እንዳከናወኑ የኅብረተሰቡ ሊቃውንት በሳይንሳዊ ትንታኔያቸው በተጨባጭ ማስረጃ አስረድተዋል ያስረዳሉም ።

ታዲያ የነበረው እውነት ይህ እንጂ በሴት የበታችነት በሚያምኑ ጭፍኖች በሚተበትቡት ተጨባጭ ባልሆነ ሃሳብ ካይደለ ፥ ሴትን ከበላይነት ደረጃ አውርዶ ምን እዚህ ላይ ጣላት ? ሴት በሁለተኛ ደረጃ እንድትታይ ያደረጋት ምን እንደሆነ ይህ ለሰው ልጅ ዕድገት ወሳኝነት ያለውን ቁልፍ ጥያቄ እንድናብሰለስል ፥ መፍትሔውንም እንድንሻ እንገደዳለን ። ምክንያቱም በኤኮኖሚ አዘቅት ውስጥ የሚዳክርን ኅብረተሰብ መንጥቆ አውጥቶ የኤኮኖሚ ነፃነቱን ለማጐናፀፍ የሴቶች ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነውና ።

ማናቸውም ነገር እንደነበረ አይኖርም ። ተፈጥሮ ያድጋል ። ያፈጃል ። ይሞታልም ። እንደገና ደግሞ ሌላ ይተካል ሥርዓተ ማኅበር የምርት ኃይል እየጨመረ ፥ ሀብት እየዳበረ የምርት መስኮች በመስፋፋታቸው ፥ በየጊዜው ሰፍነው በነበሩት አጠቃላይ ታሪካዊ ሁኔታዎች ክበብ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ማኅበራዊ የሥራ ክፍያ በማስከተሉ ፥ ከነርሱም ጋር የመደቦች መፈጠር የግል ሀብት ባለቤትነት ፅንሰ ሃሳብ ብቅ አለ ። የበዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች ተፈጠሩ ።

ከዚህም ጊዜ አንስቶ ሴት ቀንበር ተጫነባት ። ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ፈልጎ ማቅረብ ፥ የማምረቱንም ተግባር የማከናወኑና የማምረቻወችንም መሳሪያዎች በቁጥጥር ሥር ማድረጉ የወንድ መብት ሆነ ይህ ሴትን የኤኮኖሚ ጥገኛ ስላደረጋት በሁለተኛ ደረጃ እንድትታይ አደረጋት ። እንግዲህ በዚህ አኳኋን ነው የሴት እኩልነት ተሠርዞ "ዓለም አቀፍ ታሪካዊ የሴት ፆታ ድል መመታት የሆነው" ።

በግል ሀብትነት ላይ የተመሠረቱ በዓለም ላይ ያሉት ኃይሎች በሙሉ የማምረቻ መሳሪያዎች ባለቤት ያልሆኑትንና በድርብም ደግሞ ሴትን ለመበደል የሚኖሩ ናቸው ። የገዥው መደብ ለመንጠራራት ያመቸው ዘንድ የሥርዓቱ ላዕላይ መዋቅር የሆኑትን እንደሃይማኖት፥ህግ፥ባህል ወ.ዘ.ተ. ፈጠረ ። አጠናከረ ። እነዚህም ይበልጥ በሴቶች ላይ ተፈጻሚነትን አገኙ ። እዚህ ላይ በይበልጥ ሃይማኖትን በምሳሌነት በመውሰድ ለሰው ልጅ በሙሉ ለድሃውም ለሀብታሙም ፥ ለወንዱም ለሴቱም ቆሜያለሁ እያለ ሁሉንም ፍጡር በአንድ ዐይን መመልከቱን እየለፈፈ ፥ በተግባር ግን ቁልጭ ያለውን ተቃርኖ በመሥራት በተለይ በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን አድልዎ ይህም የገዥውን መደብ ምን ያህል እንዳገለገለ ብዙ መጥቀስ ይቻላል ።

ሃይማኖት ፍጹም ተፈጥሮአዊ የሆነውን የወሊድን ተግባር ከንውን ፈጻሚውን የወር አበባን እንደነውር አልፎም እንደእርኩስ ነገር ቆጥሮ ወደ ቤተ እግዚአብሔር መግባትን ይከለክላል ። ሴትን እንደርኩስ በመቁጠር ነው። ነገር ግን ከሴቷ ከማርያም ድንግል ከሥጋዋ ሥጋን ፥ ከነፍስ ነፍስን ነሥቶ የተወለደውን ልጅዋን ቅዱስ ቅዱስ ይላል። ብቻ ይህንንም ቢሉ ሌላ ከእንትትን ዘሎ በእንትን ነውና መሹለኪያ ቀዳዳ አይገኝም፤ ጉዱ ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት ሆነና ነው እንጂ ሌላም ብዙ ብዙ በጣም ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻል ነበረ ። ይቻላልም ። ቢሆንም ጥቂቶቹ እንዲህ ይላሉ በሥነ ፍጥረት በኩል ፥ ሄዋን ከአዳም ጐን ተገኘች (መጽሐፍ ቅዱስ) ሄዋን አዳምን ትረዳው ዘንድ ፈጠረለት ፤ ሰው (ሰው እዚህ ላይ ባባባላቸው ወንድ ለማለት ነው) በተፈጥሮ አዋቂ ሲሆን ከጐኑ የተገኘችው ሔዋን አሳተችው ወ-ዘ-ተ- እንዳቸውም እውነት እንደሌላቸው የተፈጥሮ ሳይንስ ያስረዳል ።

እንዲያውም ሃይማኖት ሴትን በበታችነት ለማሳየት ዓይነተኛው ላዕላይ መዋቅር መሆኑን ሞርጋን በመጽሐፉ ሲያስረዳ በኤርሜኒያ አገር በአናይቲስና በቆሮንጦስ በአፍሮዳይት ቤተ መቅደስ ውስጥ ገላን ለገንዘብ አሳልፎ መስጠት በመጀመሪያ ሃይማኖታዊ ግብር እንደነበርና ግብሩም የሚፈጸመው የፍቅር አምላክ በሆነችው ቤተ መቅደስ ሲሆን ፥ ቀደም ሲል ገንዘቡ ገቢ የሚሆነው ለቤተ መቅደሱ ግምጃ ቤት እንደሆነና በቤተ መቅደሱም ውስጥ ያገለግሉ የነበሩት ሴቶች በያዴሬ (ባይላዴራ በፖርቱጋል የሴት ዳንሰኛ ማለት ነው) ይባሉ እንደነበር በኋላም የመጀመሪያዎቹ ዘማውያት እንደሆኑ ገልጿል ። ይበልጥ የሚገርመው ደግሞ ግብሩን ለመፈጸም የተወገዘ የነበረው ለሴቶች እንጂ ለወንዶች አለመሆኑ ነው ። ይህም ምንን እንደሚያመለክት ለአንባቢ ስውር አይሆንም ። አይደለምም ።

በአርሜንያ ያን ጊዜ በነበረው የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ ሴቶችን በተገለጸው አኳኋን ይዟቸው ነበረ ። ሕብረተሰብ ታዳጊ ተለዋዋጭ ነውና ባደገ በተለዋወጠ ቁጥር ሃይማኖትም ከኅብረተሰቡ ጋር አብሮ ለመሄድ ራሱን እየለዋወጠ ፥ ቅርንጫፎቹም እየበረከቱ መጡ እንጂ ሁሉም ሃይማኖት በመሠረቱ አንድ ነው ለሥርዓተ ማኅበሩ ማጠናከሪያ የዋለ የገዥው መደብ መሳሪያ ነው ። ለምሳሌ ያህል የእስልምና ሃይማኖት ሴቶች በአደባባይ እንዳይወጡ ከወጡም ፊታቸውን እንዲሸፍኑ ያዛል ፤ ሌላውም ሃይማኖት በየበኩሉ በሴቶች ላይ የየራሱ ሕግ አለው ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የገዥ መደብ በተንሠራራበት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሃይማኖት ፥ ሕግ ባህል ወዘተ ኅብረተሰብን የማያራምድ የሥርዓተ ላዕላይ መዋቅር ናቸውና የሰው ልጅ ዕድገትና ብልጽግና ያገኝ ዘንድ መሠረታዊና ሥርነቀል የሆነ ለውጥ እንሻለን። ምክንያቱም የጠቅላላው የኅብረተሰብ ነፃ መውጣት የሴቶች ነፃ መውጣት ነውና (አለበለዚያ ግን 3 ሺህ ዓመት አልፎ ሌላ 3 ሺህ ዓመት ቢተካ ሴት አርነት አትወጣም ።) የሴት እኩልነት በተግባር ሊተረጐም የሚችለው ከጊዜዋ በጣም አነስተኛውን ለቤት ሥራ አውላ ሌላውን ጊዜዋን በከፍተኛ ደረጃ አምራች በሆነው በኅብረተ ሰብ የማምረት ተግባር ውስጥ ስትሳተፍ ብቻ ነው ። በጓዳ ውስጥ ተወስኖ የቀረውን ሥራዋን በእንዱስትሪ ደረጃ አስፋፍቶ የአደባባይ መልክና ይዞታ በመስጠት ብቻ ነው ሴትን በሁሉም ቦታ በማሰለፍ ነው ። አለዚያ ግን መዳከር ይሆናል ። ይህንንም ፈር ለማስያዝ በሚደረገው ትንቅንቅና ተጋድሎ የድርብ ተጨቋኞችንና የድርብ ታጋዮችን ትግል ድል መምታት እንቅፋት ለመሆን ሃይማኖታውያን አይዞሽ በምድር እንዲህ ቢከፋሽ በሰማይ ደጅ ታገኚዋለሽ እያሉ ትግሉን ከማኮላሸት ይቆጠቡ ከራሳቸው ቤት ጽዳት አልጀመሩምና እንላለን ።

ታሪኳ ምስክር



# የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዓምድ

## የእግዚአብሔር መሐሪነት

የእግዚአብሔር ቃል ሁለተኛ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ ፦ ተነሥተህ ወደዚያችው ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሂድ ፤ የምነግርህንም ስብከት ስበክላት አለው ። ዮናስም ተነሥቶ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወደ ነነዌ ሄደ ፤ ነነዌም የሶስት ቀን መንገድ ያህል እጅግ ታላቅ ከተማ ነበረች። ዮናስም የአንድ ቀን መንገድ ያህል ወደ ከተማይቱ ውስጥ ሊገባ ጀመረ ጮኸም ፦ በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች አለ ።

የነነዌም ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ ለጾም ነገሩ። ከታላቁም ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ ማቅ ለበሱ ። ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ ደረሰ ፤ እርሱም ከዙፋኑ ተነሥቶ መጐናጸፊያውን አውልቆ ማቅም ለበሰ ፤ በአመድም ላይ ተቀመጠ ። አዋጅም አስነገረ ፤ በነነዌም ውስጥ የንጉሡንና የመኳንንቱን ትእዛዝ አሳወጀ ፤ እንዲህም አለ ፦ ሰዎችና እንስሶች ላሞችና በጐች አንዳችን አይቅመሱ ፤ አይሰማሩም ውኃንም አይጠጡ ፤ ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ ። እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደሆነ ፥ ከጽኑ ቁጣውም ይመለስ እንደሆነ ማን ያውቃል? እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም ።

ከዚህ በላይ የተመለከተው ጥቅስ የተወሰደው ከትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 3 ፡ 1 - 10 ነው ። ስለ እግዚአብሔር መሐሪነትና ይቅርባይነት በይበልጥ ለማንበብና ለማወቅ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝተው እንዲያነቡ በትህትና እናሳስባለን ።

መጽሐፍ ቅዱስ በየመጻሕፍት መደብሮቹ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ ። በብዛትና በተለያዩ ቋንቋዎች ለማግኘት የሚችሉት ግን ከኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ነው የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኘው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አራት ኪሎ ከሐውልቱ አጠገብ ነው።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

ዋና ዓላማ

ሀ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰዎች በሚረዱት ቋንቋ ማቅረብ ፤

ለ/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰዎች ለመግዛት በሚችሉበት ዋጋ ማሰራጨት ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ አንዱን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከ$11 (አሥራ አንድ ብር) በሚበልጥ ዋጋ አሳትሞ በ6 ብር (በስድስት ብር) ብቻ ይሸጣል ። ይኸውም አንዱን መጽሐፍ ቅዱስ በሽጠ ቁጥር 5 ብር ይከሥራል ማለት ነው ። ማኅበሩም ለአገልግሎት እንጂ ለትርፍና ለንግድ ያልተቋቋመ ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ አያስፈልግም ። ከዚህም በላይ ማኅበሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በልዩ ልዩ ብሔረሰብ ቋንቋዎች ለማቅረብ የትርጉምን ሥራ ያካሄዳል ። ማኅበሩ እስከ ዛሬ ድረስ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ ፥ በኦሮምኛ ፥ በትግሪኛ ሲያቀርብ ሙሉ አዲስ ኪዳንን በአኙዋክ በኩናማና በትግሬኛ በሱማሊኛና በግዕዝ ሲያሳትም ወንጌሎችንና ክፍሎችን ደግሞ በወላይታ በአፋርኛ በቦረናና ኦሮም አቅርቧል ። በሌሎችም



www.ethiopianorthodox.org

የአገር ልሳናት ለማቅረብ የእርስዎን እርዳታና ተባባሪነት እጥብቆ ይሻል ።

ማኅበሩን ለመርዳት አጭሩ መንገድ አባል መሆን ነው ። ለአባልነትም የሚከፈለው በዓመት 5 ብር ብቻ ነው ። ለእግዚአብሔር አገልግሎት በዓመት አምስት ብር መርዳት ለአንድ ክርስቲያን የሚከብድ ክፍያ ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ?

"አንተ ግን በተማርክበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ፤ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል ። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" 2ኛ ጢሞ. 3 ፡ 14 - 17 ።

ይበልጥ ለመረዳት በፖ.ሣ.ቁጥር 30750 አዲስ አበባ ብለው ይጻፉልን ወይም በስ.ቍ. 122033 ይደውሉልን ። የባንክ ሂሳባችንም ቁጥር አራት ኪሎ ንግድ ባንክ 685 ነው ።

## ታውቃላችሁን ?

በየቋንቋዎች የሚጽፍ የጽሕፈት መሣሪያ

በብዙ ቋንቋዎችን የሚጽፍ ታይፕ በኒውዮርክ ተሠራ ። ይህም ከቻይንኛ ሌላ በ18 ቋንቋዎች መጻፍ ይችላል ። መሣሪያው ለ4.800 የቻይና ፊደላት አንድ ቁልፍ ሲኖረው ሁለተኛው ለሌሎች ቋንቋዎች የሚሠራ ነው ።

የዚህም የጽ መሣሪያ አሠራር ልክ እንደ ቻይናው የጽ መሣሪያ ነው ። በውጭ ቋንቋ በሚጽፍበት ጊዜ አሠራሩ በጣም ቀላል ነው ። በቁመናና በአግዳም አቅጣጫ ይሠራል ።

አንድ የቻይናን ፊደል ለመጻፍ ከፍተኛው ጊዜ ከአንድ ሴኮንድ ያነሰ ነው ። አንድ ፈጣን ታይፒስት በአንድ ሰዓት 3.600 ፊደላትን መምታት ይችላል ሲል የ1976 የክረምት ዕትም የኤዥያን ማሴንጀር የተባለው መጽሔት ገለጸ ።

በዓለም የሬዲዮ ጣቢያዎች ብዛት

በዓለም ባሁኑ ጊዜ 24.270 የዜና ማሰራጫ ጣቢያዎች አሉ ። ሰሜን አሜሪካ 7.470 ፣ አውሮፓ 5.980 ደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን 4.270 ፣ የሶቪዬት ሕብረት ፣ 3.030 ፣ እስያ (ሕዝባዊ ቻይናን ሳይጨምር) 2.380 ፣ አፍሪካ 550 እንዲሁም የአረብ ሀገሮች 250 አላቸው ። ይህም በቅርብ ጊዜ በዩኔስኮ የወጣው እስታትስቲክስ ነው ሲል የ1976 የክረምት እትም ኤሽያን ማሴንጀር መጽሔት ገለጸ ።

# የአርመን ኦርቶዶክስና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሚቀጥለው የካቲት ወር ውይይት ይጀምራሉ ተባለ ።

ዋሽንግተን ዲ. ሲ. በአሜሪካ የሚገኘውን የአርመን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚወክለው የሃይማኖት ቡድንና የዓለም አቀፍ የካቶሊክ ጳጳሳት በየካቲት ወር የዓለም ክርስቲያኖችን የሚወክል ውይይት ይጀምራሉ ።

ይህም ሊሆን የቻለው ከስምንት ዓመት የሃሳብ ልውውጥ በኋላ በአርመናዊው ፓትሪያርክ ቫዝጌን ቀዳማዊና በሮሙ ፓፓ ጳውሎስ አሳሳቢነት ነው ። ሲል ቍጥር 8/44/77 የሆነው ኤፒኤስ የተባለው ጋዜጣ ገለጠ ።

❖

## የቁስጥንጥንያው ኤኩኑሚካኤል ፓትርያርክ

የቁስጥንጥንያው ኤኩኑሚካል ፓትርያርክ ድሜጥሮስ አንደኛው የኦርቶዶክስና የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያናት ከ16ኛው መቶ ዓመታት ጀምሮ ያደረጉትን መንፈሳዊ ውይይቶችንና ውሳኔዎችን መርምሮ ሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት እንዲቀራረቡ ለማድረግ 20 አባላት ያሉበት ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት በኩል አንድ አጥኚ ኮሚቴ እንዲቋቋም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናትን አሳስበዋል ሲል ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጽ/ቤት የፓትርያርኩ ተወካይ ሚትራ ፖሊታን ኢሜላኖስ ከጀኔቭ መግለጻቸውን ቍጥሩ 26/77 የሆነው የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ጋዜጣ ገለጸ ።

## የሩስያ ኦርቶዶክስና የፊላንድ ሉተራን ቤተ ክርስቲያን ውይይት ለሰላም አመዘነ ።

ኪቭ የሩስያ ኦርቶዶክስና የፊላንድ ሉተራውያን የሃይማኖት ተከታዮች እምነታቸውና ሃይማኖታቸው በአዲስ ኪዳን መሠረት መሆኑን በማመን ወደ ስምምነት ደርሰዋል ።

ቀደም ብሎ የሁለቱም እምነት የተለያየ ነው እየተባለ ይነገር እንደነበር ተገምቷል ። ውይይቱም የተካሄደው በአሥሩ የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል ማህበረተኞችና በፊንላንድ ወንጌላውያን ሉተራን ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በኪቭ ሊቀ ጳጳስ ፊላሬት ጋላሺያና በቱርኩና በፊንላንዱ ሊቀ ጳጳስ ማርቲ ሲምጀኪ መካከል ነበር ሲል ቍጥሩ 27/77 የሆነው የሉተራውያን ዓለም አቀፍ ጋዜጣ ገለጸ ።

## በዓለም ክርስቲያኖች የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር በያውንዴ ስብሰባ አደረገ ።

የዓለም ክርስቲያኖች የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር ስብሰባውን ከሰኔ 21-27/69 በያውንዴ ካሜሮን ስብሰባ አድርጐ ነበር ። ስብሰባውንም በአዘጋጅነት የተቀበሉት በካሜሩን የሚገኙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

ስብሰባውም ያተኮረው በመገናኛ ዘዴዎች ሠራተኞችን ማሠልጠን እንዴት እንደሚቻል እንደነበር ቍጥሩ 20 77 የሆነው አክሽን የተባለው የማኅበሩ ጋዜጣ አስታወቀ ።



# ቤተ ክርስቲያንና እኩልነት

አንድነት ፤ እኩልነትና ወንድማማችነት" የተሠኙት ሕያዋን ቃላት በአንድነትና በሥስትነት ሲነገሩ የኖሩትና በስራም የተተረጐሙት በቤተ ክርስቲያን መሆኑን የ2000 ዓመታት ታሪክ ይመሰክራል ሦስትነት (ሥላሴነት) ካላቸው ከነዚሁ ቃላት በተለይ ዕኩልነት የተሠኘው ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ማንም ክርስቲያን የሚያደርገው መንፈሳዊ መፈክር ብቻ ሳይሆን የክርስቲያናዊ ሕይወት አቢይ መርሆ መሆኑ የማያከራክር ሐቅ ነው ።

ይህንም እንኳንስ ክርስቲያኑ ማንም አይክደውም ስለዚህ ነው የኪዩባው አብዮታዊ መሪ ፊደል ካስትሮ ሲናገር "የጥንት ክርስቲያኖች የዕኩልነት ኑሮ ረፍዶ ከመጣው መደብ አልባው የህብረተሰብ መዋቅር (ኮሚዩኒዝም) ጋር ተመሳሳይነት ነበረው" በማለት የመሰከረው ይህም አባባል በቀጥታ የሚያስረዳን በሐዋርያት ሥራ 4 ፡ 32 - 35 ያለውን የጥንት ክርስቲያኖች የኅብረተሰባዊነት ኑሮ ታሪክ ነው ።

አዎ በዚያ መደብ አልባ መንፈሳዊ የኅብረት ኑሮ በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ አንድ ልብ አንዲት ነፍስ ነበራቸው ። ከዚህም የተነሣ ይህ የኔ ነው ያ ያንተ ነው የሚባል የግል ንብረት አልነበራቸውም ፣ የአለው ንብረት በሙሉ የጋራ ነበር እንጂ ። በነርሱም መካከል አንድም ድኃ አልነበረም ምክንያቱም ለሁሉ (ለያንዳንዱ) እንደፍላጐቱ መጠን ያካፍሉት ነበር" ተብሎ ተጽፎአል ። እንግዲህ የመደብ አልባው ሥርዓተ ኑሮ መዋቅር (ሣይንሣዊው (ኅብረተሰባዊነት) የሚያውጀው መርሖ እያንዳንዱ እንደችሎታው መጠን ይሠራል ፣ በፍላጎቱም መጠን ደመወዙን (ዋጋውን) ያገኛል" የሚል ስለሆነ የጥንቱ ክርስቲያኖች በመሠረቱ የህብረት ኑሮ" ለያንዳንዱ እንደፍላጐቱ መጠን ያካፍሉት ነበር" የሚል በመሆኑ ፍጹም ዕኩልነትን የሰፈነበትን ኅብረተሰባዊነት በመገንባት ረገድ ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ እንደነበራት ዓለም አቀፍ የሆነ ታሪካዊ ሐቅ ነው ።

ነገር ግን ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የቀድሞው ሥርዓተ ማኅበር ቀዳሚ ሰማዕት በሆነው በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት በተጀመረው ስደት አማኞች ወደ ልዩ ልዩ አህጉር ሲበተኑ የአረማውያንን የየግል ሥርዓተ ኑሮ በመለማመድ የግል ንብረት የማዳበርን ባህልና ሥርዓት መውረሱ አልቀረም ይሁን እንጂ ያ የዕኩልነት የኑሮ ሥርዓት በአንድ አንድ ገዳማት ሲታይ አሁንም የሚሠራበት ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላልና ቤተ ክርስቲያን የዕኩልነትና የኅብረትን ሥርዓተ ኑሮ በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንደምትችል ይታመናል ።

በመሠረቱም ቢሆን ክርስቶስ ራሱ የክርስቲያኖችን ሥርዓተ ኑሮ የቀየሰው በኩልነት ደረጃ ነው የገዥና ተገዥ የበዝባዥና የተበዝባዥ ሥርዓት ሁሉ አረማዊ ሥርዓት መሆኑን በወንጌሉ ተናግሮአል ። ለዚህም በማቴዎስ 20 ፡ 25 - 28 "የአረማውያን ገዥዎች ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ ኃይላቸው በሕዝብ ላይ ተንሰራፍቶ ይኖራል" ነገር ግን ይህ ዓይነት ሥርዓት በናንተ መካከል መኖር አይገባውም ፤ የእናንተ አለቃ መሆን የሚፈልግ ቢኖር ተላላኪ አገልጋይ ይሁናችሁ እኔም ራሴ እንኳ ላገለግል እንጂ ልገለገል አልመጣሁም" በማለት ፍጹም ዕኩልነትን አብሥሮአል ። ሥርዓተ ባርነትና ጌትነትንም በማውገዝ ከእንግዲህ ወዲህ አገልጋዮቼ ብየ አልጠራችሁም ። ይልቁንም ወንድሞቼ ብየ" እጠራችኋለሁ በማለት አንድነትን ዕኩልነትንና ወንድማማችነትን ሰብኳል ።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ ይህ የዕኩልነትና የወንድማማችነት መንፈስ በመላው ዓለም እንዲሠፍን የሚፈለግበት ዘመን ነው ። በውዴታ መፈጸም የሚገባው ይህ ክርስቲያናዊ የዕኩልነት ኑሮ ግዴታ እስኪታከልበት መጠበቅ የለበትም። በቆዳ በአጥንት በዘር ቆጠራ በጠባብ ብሔረተኛነት ያረጀ የትምክህተኛነት ሥርዓት መለወጥ አለበት ። ማግኘትም ሆነ ማጣት ከብዙው ሕዝብ ጋር መሆን ስላለበት ለግል ኑሮ ከመስገብገብ ይልቅ በኅብረተሰቡ ጥቅም ተቀዳሚነት ማመን ፀረ ሕዝብ የሆኑትን ረኀብና ድንቁርና የመሳሰሉትን ሁሉ መደምሰሻ ኃይል ነው። ሲድኒ ኩክና ፣ ጋርት ሊን የተባሉ ሊቃውንት እንደተናገሩት "የምንመኛት አገር ወይም ዓለም ሁሉም ሰው በእኩልነት ሥራ ምግብና ቤት ሊኖረው የሚችልበትን የሰው ጠባዩና ሙያው እንጂ ቀለሙና ዘሩ ወይም አጥንቱ የማይመረጥባትን" ነውና ብለዋል፣

ለማስረጃ ያህል በባሪያና በጌታ መካከል የነበረውን ያለሕዝባዊ አመጽ የማይፈታውን ብርቱ ቅራኔ እንመልከት ይህን ቅራኔ የመላበት ሥርዓተ ማኅበር ለማፍረስና የእኩልነትን ሥርዓተ ማኅበር ለመገንባት ከጥንት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ያላደረገችው ጥረት የለም ። ነገር ግን የማናቸውም የኅብረተሰብ ዕድገት የሚወሰነው በኅብረተሰቡ ፍላጎት መጠን በመሆኑና የብዙኃኑ ድምጽ በማየሉ ምክንያት እንዲያም ሲል በኃይል ጭምር በመጫን የቤተ ክርስቲያን ድምፅ እንዳይሰማ የማድረግ ኃይልና ሥልጣን ያላቸው ኃያላን (ዲክታተርስ) በየጊዜው በመነሣታቸው በባሪያና ጌታ መካከል የነበረው ቅራኔ ሥር ነቀል ለውጥ ሳያደርግበት ቢቆይም ይህኑ ኢሰብአዊ ሥርዓተ ማኅበር በማውገዝ ረገድ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍዋን አጥፋ የተቀመጠችበት ጊዜ የለም ።

ከምታስተምራቸው ትምህርቶች መ



www.ethiopianorthodox.org

ካከል ባጭሩ "ባሪያ ወይም የጭዋ ልጅ የሚባል የሥርዓተ ኑሮ ልዩነት መኖር የለበትም ። ወንድ ወይም ሴት ተብላችሁ ሳትለያዩ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ኅብረተሰብ ናችሁ ።" የሚል ቃል ይገኛል ። ገላ. 3.28 ።

በሌላም በኩል አንዱ ሀብታም ሌላው ድኃ ሆኖ የመኖር ሁኔታ ራሱ ኅብረተሰቡ በግል ፍላጐቱ የፈጠረው የስግብግብነት ጠባዩ እንጂ ከተፈጥሮ ያልታዘዘ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ። ይህንም በማስመርኰዝ ሀብታሙ ያለደመወዝ የድኃውን ጉልበት መበዝበዝ እንደማይገባው ታወግዛለች ለዚህም ማስረጃ ቢያስፈልግ "ሀብታሞች ሆይ ኑ አልቅሱ ። እስጨናቂ መከራ ይመጣባችኋል ሀብታችሁ በነቀዝ ልብሳችሁም ብል በልቶት ተበላሽቷል ወርቅ ብራችሁም ዛገ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላዋል ። እነሆ ምድራችሁን ያረሡት ሙያተኞች ገበሬዎቻችሁ ደመወዛቸውን ቀምታችኋቸው ይጮሃሉ ። ጮኸታቸውም ከኃያሉ አምላክ ጆሮ ደርሶአል ።" የሚል ብርቱ የውግዘት ቃል አለ።(ያዕ.5.1-4)

ሌላው ማስረጃ ቢያስፈልግ "በተፈጥሮ ጓደኛህ ላይ ግፍ አትሥራ ። አትቀማው የሙያተኛው ዋጋ እስከነገ ድረስ እንኳ አይደርብህ ተብሎ ተጽፎአል (ዘሌዋ. 19 ፥ 13) እንዲሁም ድሆችን የምታስጨንቁና የምትጨቁኑ እናንተ የባሳን ሠንጋዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እናንተን በሰይፍ ከናንተ የተረፉትንም በመንጠቆ የሚመነጥቅበት ዘመን እነሆ ቀርቧል" በማለት ብዝበዛንና በዝባዦችን ያወግዛል ። (አሞጽ. 4. 1)

ይህም ሁሉ የሚያሳየው አንዱ ጌታ ሌላው ግን ባሪያ አንዱ ሀብታም ሌላው ግን ድኃ ሆኖ መኖር እንደማይገባው እያወገዘ ለሁሉም የእኩልነት ሥርዓተ ማኅበር እንዲሠፍን የነበረውንና ያለውን ወደፊትም መሆን የሚገባውን መሠረተ ለውጥ የሚጠቁም መሆኑን መዘንጋት አይገባንም ።

ስለዚህም ዋናው የቤተ ክርስቲያን ዓላማና ተግባር ሴት ወንድ ፤ ወጣት ሽማግሌ ባሪያና ጌታ ድኃና ሀብታም የሚል ልዩነት ሳይኖር ሁሉም በክርስቶስ አንድ ዓይነት ዕኩልነት እንዲኖራቸው ማድረግ መሆኑን ተገንዝበን አማኞች የሆንን ሁሉ ስለሰው ልጆች ዕኩልነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባናል ። አሁንም አንድነት ዕኩልነትና ወንድማማችነት የተሠኙት ሕያዋን ቃላት በገቢር ተተርጉመው ለዘለዓለም ይኑሩ እንላለን ።

ከቆስ መክብብ አጥናው

## በወላይታ አውራጃ አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ ተቋቋመ ።

በወላይታ አውራጃ በሰባቱ አውራጃዎች ከሚገኙት በአምስቱ ወረዳዎች አጠቃላይ የሰበካ ጉባዔ መቋቋሙን መምህር ወ/ገብርኤል ክፍሌ የዚሁ አውራጃ ሐዋርያና የደብረ መንክራት ተክለሃይማኖት ገዳም አበ ምኔት አስታወቁ ፡ በዚሁ መነሻ መምህር ወልደገብርኤል ጨምረው እንደ ገለፁት በአምስቱ ወረዳዎች በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሰበካ ጉባዔ ከመቋቋሙም በላይ በወረዳ ደረጃም በአጠቃላይ የሰበካ ጉባዔ ተቋቁሞ ሥራውን በማካሄድ ላይ የሚገኝ መሆኑን አመልክተዋል በነዚሁ አምስት ወረዳዎች 27 የሰበካ ጉባዔዎች የሚገኙ ሲሆኑ በነዚሁ ሰበካጉባዔ የሚገኙ ምዕመናንም ከአስር አንድ እንዲያዋጡ አጠቃላይ ጉባዔው ከፍተኛ ጥረት አድርጐ ይኸውም በሥራ ተተርጉሞ ከአስር አንድ መዋጮው የቀጠለ መሆኑን ጨምረው አስረድተዋል ።በተጨማሪም ከእያንዳንዱ የሰበካ ጉባዔዎች ለሥራ ማስኬጃ ከእያንዳንዳቸው $5 አምስት ብር እንዲመደብ ያደረገ ሲሆን በወር የሥራ ማስኬጃው በድምሩ $135 መሆኑን ለመረዳት ተችሏል ።

ከዚህም ሌላ ይህ አጠቃላይ ጉባዔ እየተዘዋወሩ ሥራውን የሚቆጣጠሩ ሶስት ተቆጣጣሪዎች መሾሙ ተገልጿል ። እነዚህም ተቆጣጣሪዎች ያለዕረፍት እየተቆጣጠሩ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባሉ ።

እንደዚሁም በእያንዳንዱ የሰበካ ጉባዔ 1ኛ የእንግዳ ተቀባይ 2ኛ የአስታራቂ 3ኛ የወጣቶች ሰብሳቢ ፣ 4ኛ/ የዕርዳታ ሰጭና ተቀባይ ቡድን ሲኖረው ወደፊትም ከ27ቱ የሰበካ ጉባዔ የተውጣጡ ሁለት ሁለት ሰዎች በአንድ ቦታ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮርስ እንዲደረግላቸውና ተመልሰው የክፍላቸውን አባሎች እንዲያስለጥኑ ለማድረግ እቅድ መኖሩን ሐዋርያ ወልደ ገብርኤል አስታውቋል።

እንደዚሁም በጊዜ ብዛት ያረጁ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ ፤ ንዋየተ ቅድሳትም እንዲሟሉ ፤ የካህናቱም አበል ከፍ እንዲል ጥረት የሚያደርግ መሆኑን በማብራራት ከላኩት ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል ። እንደዚሁም ቀሪዎቹ የሰበካ ጉባዔዎች በወረዳ በመደራጀት በቀጠሮ ላይ መሆናቸውን አስታውቀው እነዚሁ በቀጠሮ የሚገኙት የሰበካ ጉባዔዎች በቅርብ ጊዜ በአጠቃላይ የሚደራጁ መሆናቸውን አስረድተዋል ። ከዚህም ሌላ በእያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያናት በየሳምንቱ $05 ሳንቲም የሚሰበስቡ ድርጅቶች ተቋቋመው እነዚህም ያመረ የሥራ ውጤት በማሳየት ላይ መሆናቸው ታውቋል ። ይህ በየሳምንቱ የሚከፈለው አስተዋፅዖ በጣም ቀላል በመሆኑ ምዕመናን በሙሉ ወደዚህ ድርጅት በመመዝገብ ላይ መሆናቸው ሲታወቅ ይህም ገቢ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚውል ነው ሲሉ መምህር ወልደገብርኤል ክፍሌ አስረድተዋል ። አጀማመሩ እጅግ የሚያስደስትና ለሌሎችም መልካም አርአያ የሚሆን ነው

በወላይታ የተቋቋመው አጠቃላይ የሰበካ ጉባዔ መልካም የሥራ ፍሬ ማሳየት እንደጀመረ ሁሉ ሌሎችም ፤ የሰበካ ጉባዔዎች የዚህን መልካም ምሳሌነት ተከትለው በአጠቃላይ የሰበካ ጉባዔ ቢደራጁ የበለጠ ውጤት እንደሚያሳዩ አንጠራጠርም ።



# የኢ/ተ/ቤ/ክ/ - የልማት ኮሚሽን ለምን ተቋቋመ ?

ይህች ቤተ ክርስቲያናችን ከተመሠረተችበት ወቅት አንሥቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደኅንነትና ደስታ ከመታገል የተቆጠበችበት ክፍለ ጊዜ የለም ። የሃይማኖት ድርጅት እንደመሆኗ መጠን ነፍስን ለማርካት ያለባትን ግዴታ ስታሟላ በሌላ በኩል ደግሞ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማበርከት ረገድ ያደረገችው ተጋድሎ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን ።

## ትምህርት ፤

በራሳችን ቋንቋ ትምህርት መስጠት የተጀመረው ፊደሎቻችን እናጋሪ ምልክቶች ተበጅቶላቸው ያለምንም ችግር ማንም ሰው በቀላሉ የሚያነብበት ዘዴ የተገኘው በእንጸሩም ቋንቋ በቃላት እየበለጸገ የሔደውና ብዙ ጽሑፎችን መጻፍ የተጀመሩት ክርስትና በኢትዮጵያ በገሃድ ከተሰበከና ቤተ ክርስቲያን በኦፊሲየል ከተቋቋመች በኋላ መሆኑን የታሪክ ሊቃውንት ይናገራሉ ። እስከያዝነው ምእት ዓመት መጀመሪያ ድረስ የትምህርት ነገር ተጠቃሎ በቤተ ክርስቲያን እጅ ነበር ። ገዳማቱና ትላልቅ አድባራት እንኳን ቢቀሩ በያንዳንዱ ገጠር ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ቢያንስ ቢያንስ አንድ የንባብ ትምህርት ቤት አይጠፋም ። በሀገሪቷ 15ሺ.ህ አብያተ ክርስቲያናት አሉ እንበል ። ይህንኑ ያህል ትምህርት ቤቶች አሉ ማለት ነው ። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በማእከላዊ ግምት 15 ተማሪዎች ብንመድብ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ የምታሰለጥነው የሰው ኃይል ወደ 225 ሺ.ህ ይሆናል ማለት ነው ። በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን የትምህርት መሳተፊያ ገበታ ሁና ለ16 ምዕት ዓመታት የቆየች መሆኗ እሙን ነው ።

## ሥነ ጽሑፍ ፤

ቤተ ክርስቲያናችን የትምህርት ገበታ ናት ካልን የሥነ ጽሑፍ መደብር መሆኗ አያከራክርም ። የሃይማኖት መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ፤ የሂሳብ (ባሕረ ሃሳብ) ፤ የፍልስፍና የሕግና የመሳሰሉትን መጻሕፍት ግማሾቹን ተርጉማ ሌሎችንም ጽፋ አቆይታለች ። የኢትዮጵያን የሥነ ጽሑፍ ክምችት በሚገባ በመንከባከብ ፤ እንዳይጐሳቆሉ ማኅደር በመስፋት እንዳይጠፉ በብዙ ቅጂዎች በማባዛት ፤ በዘመነ ስደትና ጦርነት ጊዜም ወደማይደፈር ዋሻና ወደማይወጣ ተራራ በመሸሸግ ከኛ እንዲደርሱ አድርጋለች ። በአጭሩ ዛሬ ኢትዮጵያ አለኝ የምትለውና ለዓለም ለትርኢት የምታቀርበው በእንዲህ ዓይነት ዘዴና ጭንቀት የቆየውን ሥነ ጽሑፍ ነው ። ከዚህም በቀር በእንዲህ ዓይነት እደ ጥበብን በማስፋፋትና የታሪክ ቅርሶችን ጠብቆ በማቆየት ቤተ ክርስቲያናችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ባለውለታ ነች ።

## በማኅበራዊ ኑሮ ፤

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኅብረተ ሰብአዊት መሆኗን በተግባር አረጋግጣለች ። ማናቸውም የማኅበራዊ አገልግሎት ሲፈጸም የኖረው በቤተ ክርስቲያን አካባቢና ቅጽር ግቢ ነው ። ቤተ ክርስቲያን የእርቅ ፤ የመተዋወቂያና የመዝናኛ አውድማ ፤ የጡረታና የሕክምና ቤት ፤ በቀውጢ ቀንም መቀነት ሆና መቆየቷን ሁላችንም የምናውቀው ስለሆነ ሰፊ ኃተታና ማስረጃ የሚያስፈልገው አይደለም ።

ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሕዝቡ ተለይታ ከጦር ወደኋላ ያለችበት ጊዜ የለም ። ይኸንን ሀቅ የሚያስተባብል ካለ ከሐዲ ይባላል ።

ከዚህም ሁሉ በላይ ቤተ ክርስቲያን የአንድነት አውታር በመሆን አስተባብራን ኖራለች ። እንግዲህ የዚችን የናት ቤተ ክርስቲያን ውለታ የምንከፍላት እንዴት ይሆን ? ።

## የኮሚሽኑ መቋቋም ፤

ከላይ የተዘረዘረውን አገልግሎት በአዲስ መልክ ለዘመኑ በሚስማማ መንገድ ለመቀጠል ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ታኅሣሥ 26 ቀን 1964 ዓ.ም. በነጋሪት ጋዜጣ ታውጆ ተቋቋመ ። በነጋሪት ጋዜጣው መሠረት የልማት ኮሚሽን ሲቋቋም የሚከተሉት አላማዎች ነበሩት ፤

ሀ. ወጣቶች ተፈላጊ በሆኑ የሙያ ትምህርቶች እንዲሠለጥኑ ማበረታታትና መርዳት ፤

ለ. ነዳያንን መርዳት ፤

ሐ. በጠቅላላው ለትምህርት ፤ ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ልማት በሚደረገው ብሔራዊ ጥረት ተካፋይ መሆንና መርዳት የሚሉ ነበሩ ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት ኮሚሽኑ በአዋጅ በዚህ ዓ.ም. ቢቋቋምም ለጽ/ ቤቱ የተፈቀደ ባጀት አልነበረም ። የተወሰነም በጀት በርዳታ ካገኘ በኋላ ተገቢው ሰው በተገቢው ቦታ ላይ ባለመመደቡ በአንድ ዋና ሥራ አስኪያጅና በአንዲት ጸሐፊ ሲንጠላወዝ አንድ ዓመት እንዳሳለፈ ሪፖርቱ ያስረዳል ።

## የገንዘብ ምንጭ ፤

በነጋሪት ጋዜጣው መሠረት የልማት ኮሚሽን የገንዘብ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ. ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ፤

ለ. የኮሚሽኑን ሥራ ለማስፈጸም



www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ሥራ አስፈጻሚው ክፍል በሚያቀርበው ግምት መሠረት ኮሚቴው ከአጸደቀ በኋላ ከቤተ ክህነት የሚፈቀድ በጀት ፤

የሚሉ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠ/ጽ/ቤት እስካሁን የረዳው ነገር ቢኖር ቢሮ መስጠት ብቻ ነው ።

ቢሆንም ኮሚሽኑ የራሱ የሆነ ምንጭ ለመፍጠር ሙከራ አድርጎ ነበር ። ከላይ እንደተገለጠው ኮሚሽኑ ከሀገር ውስጥ የተፈቀደለት በጀት አልነበረም ። ለነዚያውም ጥቂት የጽ/ቤቱ ሠራተኞች እንኳ የሚከፈለው ደመወዝ ከውጭ የተገኘ ርዳታ ነበር ። ስለዚህም ኮሚሽኑ ሁልጊዜ ከውጭ ርዳታ ጠያቂ ለመሆን እንዳይገደድና የውጭ እርዳታው ባልታወቀ ጊዜ ሊቆም እንደሚችል በመገንዘብ ራስን የሚያስችል የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን ከርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አጥንቶ ከፍ ያለ ገንዘብ ርዳታ አገኘ ። በዚህም ገንዘብ ፤

1. መናገሻ ላይ የከብት እርባታ ሥራ፤

2. ከአዋሽ ሸለቆ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የእርሻ ልማት ፤

3. በጐንደር ክፍለ ሀገር በሰቲት ሁመራ የእርሻ ልማት ፤

4. በጉደር የእርሻ ልማትና ሌላም እቅዶች አቋቋመ ። በርከት ያለ ገንዘብ ካወጣባቸው በኋላ ገሚሶቹ በጅምር ቀሩ ፤ ሌሎችም ልማቶች በልዩ ልዩ ምክንያት "ላም አለኝ በሰማይ" ሆነው በመቅረታቸው ኮሚሽኑ ተመጽዋች ሆኖ ይገኛል ኮሚሽኑ ምን እንደሠራና እንደሚሠራ ወደፊት በተከታታይ እና ቀርባለን ።

ይቀጥላል

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1. ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ 1 ተሰ.ም. 1 ቁ. 21

2. ከሰማይ ወንጌልን የሚለይ መልአክ ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን ገላ.1-8

3. ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኢሳ. 1. 18

4. እንደ ዕባብ ብልኆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ማቴ. 10. 16

5. አንተ የምትተኛ ንቃ ክርስቶስ ያበራልሃል ኤፌ. 5. 14

6. እግዚአብሔርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ኢ.ሳ.55 6 - 7

7. በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ መክብብ . 12. 1 - 8

8. ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት አይሁን ማቴ. 24. 20

9. ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጅ ደስ የሚያሰኝ አይደለም ዕብ. 12 . 11

10. ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል በብትር ብትመታው አይሞትምና ምሳ. 23. 13


ማሳሰቢያ

1ኛ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት "ድምፀ ተዋሕዶ" የተሰኘ ጋዜጣ ከአሁን በፊት ለ14 ዓመታት ያህል እያሳተመ ለምእመናን እንዲዳረስ ሲያደርግ ቆይቷል ።

አሁን ግን በይበልጥ ከመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ጀምሮ በማኀበርተኝነትም ሆነ በበዓላት ቀን ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚዳረስበትን መንገድ በማጥናት ላይ ስለሆነ ይህንን ማሳሰቢያ የሚያነቡ ሁሉ አስተያየታቸውና ትብብራቸው እንዳይለየው ያሳስባል ።

2ኛ/ መንፈሳውያን መልእክቶችን መንፈሳውያን የሆኑ ዘመናውያን መዝሙሮችንና ጥንታውያን ዜማዎችን በካሴት እየቀረፀ ካሴት ለሚያቀርቡ የካሴት ዋጋ 5 የአገልግሎት ደግሞ 2 ብር ብቻ እያስከፈለ የሚሰጥ መሆኑን በድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣችን ማሳሰባችን ይታወሳል ።

አሁንም በዚሁ ሁኔታ የቀጠለ መሆኑን እንገልጣለን ።



አድራሻችን አራት ኪሎ ብሔራዊ ሸንጐ ፊት ለፊት
የስልክ ቁጥር 11 - 66 - 16
የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ



# ቤተ ክርስቲያንና አላማዋ

በአንድ ነገር ማመን የተጀመረው ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ ሲሆን፣ እስከዚህ ዘመን ድረስ የሆነውንም ሁሉ ስንመለከት ማንም ሰው ያለ ሃይማኖት መኖር የቻለበት ጊዜ የሌለ መሆኑንና እንዲሁም አምልኮትን በግለ ሰብእ ፣ በቤተ ሰብእ ፣ በጎሳ ፣ በነገድ ፣ በብሔረ ሰብእ ፣ በብሔር ፣ በክፍለ ዓለም ከዚያም አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመመሥረት በሰው ልጅ የሕይወት ታሪክ የቱን ያህል ጥረትና ድካም የተደረገ መሆኑን ከሃይማኖት ታሪክ መረዳት ተችሏል ።

ከክርስትና በፊትም ሆነ በኋላ በየጊዜው የነበሩት ያሉት የእምነታቸው የሕግ አቋምና ስነ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት እንደየእምነታቸው አምላካቸውን የሚቀድሱበት፣ የሚያወድሱበት ለአምላካቸው መሥዋዕት የሚያቀርቡበት በአቀማመጡ ከፍተኛና ጫካ የሆነ እንዲሁም ጸጥታና ልምላሜ ያለው የሚያስደስት ቦታ መምረጥና ማግኘትግዴታቸውና ፈቃዳቸው ነበር ።

ለምሳሌም ያህል ጥንታውያን አሲሮ ባቢሎናውያን ልምላሜ በአልተለየው በአስደሳች መስክ እየተሰበሰቡ ለአምላካቸው ይሰግዱ እንደነበር ።

ፒርሺያኖችም ፣ በየቤቱ ጣራ ላይ በሚገኝ ልዩ ክፍል ለጣዖታቸው ይንበረከኩ እንደነበር ጃፓ-ዳኞችም በተራራዎች አናት ላይ እየተሰበሰቡ ለሚያኑበት ነገር አምልኮታቸውን ይፈጽሙ እንደነበር ፤

ጥንታውያን ጋሊካኖችና እነርሱንም የመሳሰሉት ቸልሲዎች ውሃ ከሚፈልቅበት ጥቅጥቅ ካለ ጫካ እየተሰበሰቡ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ያደርጉ እንደነበር ።

አሕዛብ (ፓጋኖች) ከአማልክቱ ጋር የሚያገናኛቸው ለአማልክቱ የቀረበ መስሎ በሚታያቸው ቦታ አምልኮታቸውን ይፈጽሙ እንደነበር ፣ ከጊዜ በኋላ በመሻሻል መቅደስና መንበር መሥራት መጀመራቸውን ፣ በዚሁ ዓይነት ጥንታዊያን ግሪካኖች አምልኮታቸውን ለሚፈጽሙበት ልዩ ስም በመስጠት "ቴዎካሊ" (ቤተ እግዚአብሔር) በማለት ይጠቀሙበት እንደነበር ፣ ዕብራውያንም አምልኮት የሚፈጽሙበትን ቤተ መቅደስ ፣ ምኵራብ ማለታቸውን ክርስቲያኖችም እንደእኛ አጠራር "ቤተ ክርስቲያን" እንደግሪኮች "ኤክሊሲያ" እንደሮማውያን "ቢሲሪክ" እንደፈረንሳዮቹ "ኢግሊዝ" እንደጀርመኖቹ "ኪርሂ" እንደ እንግሊዞቹ "ቸርች"ና የመሳሰሉት መሆናቸውን ፣ እስላሞችም የአምልኮት ሕንፃዎችን "ምስኪ መስጊድ" እንዲሁም በሌሎች በኩል ሌላ ዓይነት ስያሜ እየተሰጠው መጠራቱን የሃይማኖት ታሪክ ያስረዳናል ።

ኦሪት ዘፍጥረት የሁሉንም ነገር አጀማመር የሚነግረን ልዩ መጽሐፍ መሆኑን እንረዳለን ፣ እግዚአብሔር ክብሩን የሚወርስ ፣ ስሙን የሚቀድስ ፣ ሰው በሥላሴ አርአያና አምሳል በሰብአዊ ደረጃ ልዩ ፍጡር አድርጎ የፈጠረው በወንድና በሴት የአንድነት አቋም መሆኑን በዚሁ ከላይ ከተጠቀሰው ከሙሴ መጽሐፍ መረዳት ስንችል ፣ ቅዱስ ጳውሎስም ይህኑ መነሻ በማድረግ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ ከፍቅርና ከመታዘዝ በሚመጣ አንድነት እንደሚኖርና ባልና ሚስትም በዚሁ ዓይነት ምሥጢር መኖር እንዳለባቸው ይገልጻል ።

ከጊዜ በኋላም ሰፍቶና ጎልቶ የታየው ኅብረተ ሰብእ ከዚያ ደረጃ ያደረሰው ያ የመጀመሪያ ሰው መነሻ የሆነው የወንድና የሴት አንድነት ነበር ። ያም አንድነት በመጀመሪያ መልካም እንደነበር በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ 2 በቁ. 24-25 በሚገኘው ዐረፍተ ነገር ተገልጿል ።

በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 4 እንሥቶ ያለው ጽሑፍ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው አንድነት በመቋረጡ ወንድም በወንድሙ ፣ ነገድም በነገድ ፣ ላይ ሌላውም እንደዚሁ አንዱ በአንዱ ላይ እንደተነሣና እንዲሁም ለሰው አገልግሎት የተፈጠሩት ለምሳሌ እንደ እሳትና ውሀ የመሳሰሉት ሁሉ በሰው ሕይወት ላይ ልማትንና ጥፋትን ለማምጣት መቻላቸውን ያሳያል።

ስለዚህ በእግዚአብሔር የተመረጠው ሕዝብ ታሪክ ከላይ በተገለጸው መሠረት መታየት ይኖርበታል ። ይህም ማለት የሰው ልጅ ሁሉ አጥፊ እንደመሆኑ እግዚአብሔር የሰውን ዘር በኃጢአቱ ጨርሶ ይጠፋ ዘንድ እንዳልተወውና ከዚያም በሚከተለው ረጅም የታሪክ ጉዞ ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ የኃጢአትንና የሞትን ቅጣት በራሱ ላይ ለመሸከም እስከ መጣበት ድረስ እግዚአብሔር ሕዝቡን በትዕግሥት እየመራ በኅብረት ለአንድ ዓላማ ለንስሐ ማዘጋጀቱን የሚያሳይ ነው ።

እኛ በቋንቋችን ቤተ ክርስቲያን ስንል ፣ ሌሎችም በየቋንቋቸው እንደዚሁ ሲሉ ከዚህ ላይ በሁላችንም አጠራር ሕንፃውን ብቻ ማለታችን ሳይሆን ፣ ሕንፃውንና ሕንፃውንም ከመሰለው ጋር በሕንፃውና በሚመስለው የተሰበሰበውንና ማኅበረ ክርስቶስ ማለታችን መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንችላለን ።

ይህም ከእስራኤላውያንና ከግሪኮች አጠራር ሲያያዝ የመጣ ይመስላል ። እሥራኤላውያን አቋማቸውና ዓላማቸው በሕግ አማካይነት በእምነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በማንኛውም ቦታና ጊዜ አንድነታቸውንና ሕይወታቸውን የሚመራ እግዙአብሔር ብቻ መሆኑን ደኅና አድርገው ስለሚያውቁ ፣ በሕይወታቸው ተቀዳሚ የሚያደርጉት ነገር አምልኮተ እግዚአብሔርን ስለነበር ፣



www.ethiopianorthodox.org

ቅድስናቸውን ለመጠበቅ ለሚያደርጉት ሃይማኖታዊ ጉባዔ ፣ ግሪኮችም የእነርሱ ያልሆነ ጠጉረ ልውጥ ሰው ሲያዩና ሲመለከቱ ያንን ሰው በክፉ ዓይናቸው ተመልክተው እርሱን ለማጥናት ጉባዔ ከማድረጋቸው ጋር ግንኙነት እንዳለው ሁኖ የኅብረት ጉባዔዎች አመጣጥ ትርጉም ከእነርሱ የተወረሰ ይመስላል ።

በሌላ በኩል ግሪኮች በድሮው ዘመን ለሕዝብ የሚጠቅም በማኅበር ለመሥራት ሲያስቡ የማኅበራቸውን ስያሜ “ኤክሊሲያ” በሚለው ግሪካዊ ቃል ይጠቀሙበት ነበር ይባላል ። ትርጉሙም በዚያን ጊዜው አባባል “ጥሪ” ማለት ነው ይላሉ ።

በግሪክኛ “ኤክሌስያ” የሚለው ቃል በእብራይስጡ “ክናል” ወይንም “ኢድሃ” ማለት እንደሆነ ይነገራል ።

በዚህም ስያሜ ይጠራ የነበረው ማኅበር በእግዚአብሔር ስም እንደተደረገ ሁኖ የተባረከ ስብሰባ እንደነበር ይተረካል ። “ክሃል” ወይንም “ኢድሃ” የተባለው የዕብራይስጡ ቃል በአንድነት ንስሐ መግባት በሚል ትርጉምም የታወቀ መሆኑ ይሰማል ። ይኸውም ለአንድ ዓላማ የተጠራና የተመረጠ ሕዝብ የአንድነት ወይንም የኅብረት ጉባዔ እንደማለት መሆኑም ይተረካል ።

እንደግሪኮቹ አስተሳሰብ “ኤክሊሲያ” ለሚለው ትርጉም ቃሉ አሁን ለሚጠራበት ዓላማ ከፊተኛው የኋለኛው ተስማሚ ስለሆነ ፣ የትክክለኛ ትርጉሙ አመጣጥም ከዚሁ ከሁለተኛው መሆኑ ይታመንበታል ። በእኛ አባባልም ትርጉሙ በጣም የራቀ ሊሆን ይችላል ።

የእያንዳንዱ እሥራኤላዊ ሕይወት በሕግ አማካይነት በእግዚአብሔር ይመራ እንደነበር ከታሪካቸው መረዳት የሚቻል መሆኑን ቀደም ብለን የሰማን ሲሆን ፣ በዚሁ መሠረት ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሁኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ በቅድስት ሀገር በነበረበት ጊዜ እንደማንኛውም እሥራኤላዊ ሕገ ኦሪቱን በመጠበቅ በየቤተ መቅደሱና በየምኩራበ አይሁድ እየተገኘ ማኅበራዊ ሥርዓተ ጸሎትን ፈጽሟል ፣ ትምህርትም ሰጥቷል ።

(ማቴ ም. 21 ቁ. 12-13 ፣ ማር. 11 ቊ. 16—17 ፣ ሉቃ . 19 ቊ. 45 - 56 ዮሐ. 2 ቊ. 14-17 ፣ ማቴ. 13 ቊ. 54፣ ሉቃ. 4 ቊ. 16-17) ነገር ግን ስለግሉ ጸሎትና አንዳንድ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው በየቤተ መቅደሱ ወይንም በየምኩራቡ ሳይሆን በሌሎች ልዩ ልዩ ቦታዎች መሆኑንም ከሐዲስ ኪዳኑ መረዳት እንችላለን ። (ሉቃ. 22 ቊ. 12 - 20 ቊ. 39 - 45)

## የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

የቤተ ክርስቲያን መሥራች ክርስቶስ ሲሆን ንብረትነቷም የክርስቶስ ነው፤

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በደሙ ሲመሠረታት ለጊዜው በአንድ መቶ ሃያ የክርስቶስ ቤተ ሰብእ አንድነት መሆኑን ከሐዲስ ኪዳኑ ወይንም ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረዳት ይቻላል ።

እንደገናም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በሃምሳኛው በዓረገ በአሥረኛው መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደ ዕለት ከመንፈስ ቅዱስ በተገኘው በረከትና ኃይል የቤተ ክርስቲያን መሠረት መጽናቱን በሐዋርያት ሥራ እንመለከት ።

በዚሁ ዕለት የማኅበረ ክርስቶስ የአባላት ቁጥር ከአንድ መቶ ሃያ ወደ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ከፍ ማለቱን እንረዳለን ።

እነዚህም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተመልተው ሞገስን አግኝተው እግዚአብሔርን በማመስገን ዓላማቸውን አውቀው፤ አንድነታቸውን አጽንተው አንድ በሆነ የፍቅር “አጋፒ” (የኅብረት ዳቦ) ቆርሶ በመመገብ በሕዝቡ ፊት ሁሉ መመላለሳቸውንና እግዚአብሔርም የክርስቲያናትን ቁጥር ለቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ ይጨመር እንደነበር ከሐዋርያት ሥራ መረዳት እንችላለን ። (የሐ. ሥራ 2 ቁ. 47)

የመጀመሪያው የማኅበረ ክርስቶስ ቁጥርም በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ ከስምንት ሺህ በላይ ሆነ ። እነዚህም በየጊዜውና በየደረሱበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሞቶ መነሣት ላላወቁ ሁሉ በማስረዳታቸው በሐዋርያት ስብከት መስፋፋት ምክንያት ክርስቲያናት በልሆኑ አይሁድና በክርስቲያናት መካከል አለመግባባትና ታላቅ ክርክር በመፈጠሩ በዚሁ ምክንያት የክርስቲያናት ስደት መጀመሩን ከታሪክ መረዳት እንችላለን ።

ይህም የስምንት ሺህ ክርስቲያናት ለክርስቶስ መንግሥት መስፋፋት ማለት ስደት ለስብከት ወንጌል መዳረስና ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት መልካም አጋጣሚ ጊዜ መሆኑንም በግልፅ እንረዳለን ።

በዚያን ጊዜ የነበረው የክርስቲያናት አንድነት በመንፈስ ቅዱስ የታነፀ ስለነበር ምንም ዓይነት በደል ሳይፈጽሙ ስለመልካም ሥራቸው ብቻ የሚመጣባቸውን ሥቃይና መከራ በትዕግሥት በመቀበል ስለክርስቶስ ፍቅር በሰማዕትነት ለማረፍ የወሰኑና የቆረጡ ፣ በዚህም ውሳኔያቸው መሠረት በሰማዕትነት ማረፋቸውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳናል ።

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያናት የተቀደሰ ዓላማ ስለነበራቸው በየዋሻውም ሆነ በየጉድባው ፣ እንዲሁም በየካታኰንሺው በግልጥም ሆነ በሥውር አምልኮታቸውን በመፈጸም ይኖሩ እንደነበረ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መረዳት ተችሏል ።

በዚሁ መሠረት የመጀመሪያይቱ የአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዓላማም ግልጽ ነበር ።

## በመ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ትርጉም

የሐዲስ ኪዳን መነሻ ብሉይ ኪዳን ከሆነ ፣ አንዱ መነሻ ሁለተኛው መድረሻ ሲሆን ፣ ሁለቱም በቋንቋ ትርጓሜ በቃላት አጠቃቀምና ፍች ፣ በምሳሌ ይወራረሳሉ ፣ ይቀራረባሉ ማለት ነው ።



በዚሁ መሠረት በኦሪት ዘሌዋውያን 23 ቁ. 3ላይ “-------ግን ሰባተኛው ዕለት የዕረፍት ሰንበት ስለሆነ ፣ የተቀደሰ ጉባዔ ይሆንለታል ----------” ይላል ።

እንደዚሁም በሐዋርያት ሥራ 7 ቊ. 38 ላይ “ይህ ሰው በደብረ ሲና ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ነው ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ -------” ይልና አሁንም በይቀጥላል በሐዋ. ሥራ ም. 19. ቊ. 39. ላይ “--------ግን አንዳች ብትፈልጉ በተደነገገው ጉባዔ ይፈታል” በማለት ይናገራል ።

ከዚህ ላይ ጉባኤ (ማኅበር) የሚለው ቃል ተብሎ እንደተገለጸው በዕብራይስጡ “ክሃል” ወይንም “ኤድሃ” በግሪክኛው “ኤክሊስያ” ከሚለው ቃል ጋር በትርጓሜም ሆነ በዓላማው ተስማሚና ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል ማለት ነው ።

“ኤክሊሲያ” በግሪክኛው በእኛ “ቤተ ክርስቲያን” የሚለው ቃል በአንድ ክፍለ ሀገር ፤ በአንድ ሀገር ፣ ወይንም በዓለም አቀፍ ደረጃ በማኅበረ ክርስቶስ አቋም ለነበሩ ለአሉና ለሚኖሩ ክርስቲያናት ሁሉ በአንድነት የመጠሪያ ስማቸው መሆኑን ከሐዲስ ኪዳኑ እንደሚከተለው እንረዳለን ።

በማቴ. ም 16 ቊ. 18 ላይ “-----አንተ ጴጥሮስ ነህ ፣ በዚህችም አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፤ የገሃነም ውሰድ ፣ እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት ፣ ቤተ ክርስቲያንንም እንደአረመኔና እንደቀራጭ ይሁንልህ’ ይላል ።

በሐዋ. ሥራ ም. 5 ቁ. 11 ላይ “በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ” ይልና ስለዚሁ ሁኔታ በይቀጥላል በሐዋ. ሥ. 8 ቊ. 1 ላይ “በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ ---------” ይላል ።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ቊ. 28 ላይ “እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን ፣ ሁለተኛም ነቢያትን ፣ ሦስተኛም አስተማሪዎችን ፣ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ እርዳታንም ፣ አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳናትንም አድርጓል” ሲል በተወሰነ ቦታ ላሉት ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን ፣ ዓለም አቀፍ የሆኑት ክርስቲያናት በአንድነት የተጠሩበትና የሚጠሩበት መሆኑ ነው ።

ቤተ ክርስቲያን በሚለው ቃል በየቦታው ያሉ ክርስቲያናት ሲጠሩበት” በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ------” ይላል ። (1ኛ ቆሮ 1 ቊ. 2/ ። በዚሁ ዓይነት በይቀጥላል “ከሰዎች ወይንም በሰው ያልሆነ ፣ ጳውሎስ ከእኔም ጋር ያሉት ወንድሞች ሁሉ ወደገላትያ አብያተ ክርስቲያናት” ይላል (ገላትያ 1 ቊ. 2) ። አሁንም በይቀጥላል “ጳውሎስና ስልዋኖስ ፣ ጢሞቴዎስም በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደምትሆን ወደተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን” ይላል (1ኛ ተሰሎ. 1 ቊ. 1) ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የሰማነው በየቦታው በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙትን ክርስቲያናት በአንድነት አጠቃሎ የሚጠራ መሆኑ የማያጠራጥር ግልፅ የሆነ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስን አካል አድርጎ ሲናገር “አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል ስለአካሉም ማለት ስለቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ” ይላል ። (ቆላስይስ 1 ቊ. 24)

አሁንም እንደበፊተኛው “እናንተም (ክርስቲያናት) የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ ይላል” (1ኛ ቆሮንቶስ 12 ቊ. 27)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ ሙሽራ አድርጎ ሲናገር “----እንደንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና” ይላል(2ኛ ቆሮ.11 ቊ. 2) ከዚህ ላይ እናንተ የሚለው ቃል ክርስቲያናትን ወይንም ቤተ ክርስቲያንን መሆኑ ግልጽ ነው ። ይኸው ሐዋርያ ስለዚሁ በይቀጥላል “---ይህም ምሥጢር ታላቅ ነው እኔ ግን ይህን ስለክርስቶስ ስለቤተ ክርስቲያን እላለሁ’ ይላል ። (ኤፌ. 5 ቊ. 32)

ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ወይንም ክርስቲያናትን የክርስቶስ ቤተ መቅደስ መሆናቸውን ገልጾ ሲናገር የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ሆናችሁ ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖራችሁ አታውቁምን ? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል ። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው ፣ ያውም እናንተ ናችሁ ” ይላል ። 1ኛ ቆሮ 3 ቊ. 16 - 17)

ስለዚህም በይቀጥላል “የእግዚአብሔር መንፈስ ከጣዖት ጋር ምን ግንኙነት አለው ? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና ” ይላል ። 2ኛ ቆሮ. 6 ቊ. 16) አሁንም ስለዚሁ ሲናገር “በሐዋርያትና በነቢያት መሠረትነት ላይ ታንፃችኋል የማዕዘንም ራስ ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ፣ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል ፣ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ” ይላል (ኤፌ. 2 ቊ. 20-22

ከዚህ በላይ በተነገረው መሠረት ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ወይንም በመጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ትርጉም ከሚለው እንደተረዳነው ፣ የያዕቆብ ልጆች በአባታቸው ስም ቤተ እሥራኤል እንደተባሉ ሁሉ እንዲሁም የክርስቶስ ቤተ ሰብእ ሁሉ በክርስቶስ ክርስቲያን ፣ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መባሉን በመጠኑ ለመረዳት ችለናል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ዓላማዋ

ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር አምነው በቅድስት ሥላሴ ስም ለተጠመቁ ሁሉ መጠሪያ ስማቸው፤በምሥጢት/ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር አፈጻጸም መሠረትም እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ፣ ምዕመናንም ከእግዚአብሔር በረከትን ፣ ድኅነትን ፣ አንድነትን የሚያገኙባት አንዲት ቅድስት የመድኅ ድርጅት ስትሆን ፣ ቤተ ክርስቲያን የአንድ ሰው ፣ የአንድ ነገድ ፣ የአንድ ጎሳ ፣ ሀገር ፣ በአንድ ክፍለ ዓለም የሚኖር ሕዝብ ብቻ አይደለችም ። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያናት ለሆኑት ሁሉ የአንድነታቸው መጠሪያ ናት።

ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት ፣ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት ፣ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ክርስቶስ ናት ፣ በቤተ ክርስቲያን የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም የምዕመናን ቋሚ ሕይወት ነው ። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የማይፈጸምበት የጸሎት ቤት እንጂ ቤተ ክርስቲያን አትባልም ፤ ምክንያቱም የአንድነትና የድኅነት ምሥጢር የሆነው ምሥጢረ ቁርባን ስለማይፈጸምባት ነው ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በነፃነት ፤ በእኩልነት ፣ በአንድነት ፣ ለሰላም ሁኖ የምታስተምረውም ነፃነትን ፣ እኩልነቱን ፣ አንድነትን ፣ ሰላምን ፣ ድኅነትንና የመሳሰሉትን ሲሆን የነገድ ፣ የጐሳ ። የቋንቋ ፣ የቀለም ፣ የፆታ ፤ የዕድሜና የመሳሰሉትን ልዩነት ሳታደርግ በራስዋ ሕግና ስነሥርዓት የምትተዳደር ሁና እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል የተቋቋመች የክርስቶስ ቤት ናት ። (ማቴ. 21)

ቤተ ክርስቲያን ሦስት ዓይነቶች የክህነት ማዕርጋት ባላቸው የምትመራና የምትገለገል ናት ። ይህም በበለጠ የጎላውን መናገር እንጂ የክርስቶስን ወይንም የቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ሁሉ በየደረጃው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው ።

ሦስት ዓይነቶች ያልኳቸውም ዲቁና ቅስና ፣ ኤጲስ ቆጶስነት (ጵጵስና) ናቸው እነዚህም የቤተ ክርስቲያን ሕግ በሚያዝዘው መሠረት ተመርጠውና በኤጲስ ቆጶስ ተሹመው ነቀፋና ዘለፋ በሌለበት ንጹሕ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን ይመራሉ ፣ ያገለግላሉ ።

"በምድር ያሠራችሁት በሰማያት የታሠረ ፣ በምድር የፈታችሁት በሰማያት የተፈታ ይሁን (ማቴ. 18 ቍ. 18 በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያን በኤጲስ ቆጶስ (በጳጳስ) እየተመራች በአንድነቷ ጸንታ ትኖራለች።

ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት

የቤተ ክርስቲያን መሥራች አንድ ቅዱስ ጌታ መሆኑን ከተረዳንና ከአመን ቤተ ክርስቲያንም እንደእርሱ አሐቲ ቅድስት ናት ።

በአራተኛው መቶ ዓመት በአንደኛውና በሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ ጉባዔዎች ማለት እንደሌሎቹ ዘመን አቆጣጠር በ325ና በ381 ዓ.ም. በኒቂያና በቁስጥንጥንያ የተሰበሰቡት 318ና 150 ቅዱሳን አበው "ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኩሉ ጉባዔዘሐዋርያት'' በሁሉም ዘንድ ከሁሉም በላይ በሆነችና በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን በማለት በአንድ ድምፅ የወሰኑትን እኛ ኢትዮጵያውያን የዕለት ጸሎታችን አድርገን ከማዘውተራችን በላይ እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ማለት እንደ ግሪኮችና መሰሎቻቸው ሁሉ በጸሎተ ቅዳሴያችን በተለይም በክርስቲያኖች ጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ሰው ሲነበብ ግን እኛ በአንድነት ማለት በቤተ ክርስቲያን ያለነው ሁሉ እንዘምረዋለን ። ጊዜ ካጠረንም እንደዚያው በአንድነት እናነበዋለን ።

በሦስተኛው መቶ ዓመት ገደማ የነበረ አንድ አፍሪካዊ ቅዱስ አባት ቅዱስ ቺፕሪያን በ200 ዓ.ም. ገደማ በካርታጄ የተወለደ "ቤተ ክርስቲያን መርፌና ክር ወይንም የስፌት መኪና ባላያትና ባልነካት ከላይ እስከታች አንዲት ሥረ ወጥ በሆነች በክርስቶስ ሸሚዝ የምትመሰል ናት'' ይላል ። ከዚህም በማያያዝ "በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ድኅነት ማግኘት አይችልም" ከአለ በኋላ ይኸው አፍሪካዊ ቅዱስ አባት ከዚሁ በማያያዝእንአፋረዲቢሪክ ኑየስቲ ምንቱይሬ'' ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት የለም) ብሏል ።

የዚህ ቅዱስ አባት አባባል የክርስቶስ እንደራሴ ሁኖ ቤተ ክርስቲያንን የሚመራት ኤጲስ ቆጶስ ስለሆነ በእርሱ አመራር መሠረት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ካልተፈጸመባት የምዕመናን ድኅነትና አንድነት የለም ማለቱ ይመስላል ።

በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ በእምነት ፣ በተስፋ ፣ በፍቅር የተመሠረተ ሁኖ ሁሉንም በማስተማር ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም እግዚአብሔርንና ሰውን በማገልገል በአንድነት ፣ በነፃነት ፣ በእኩልነት ፣ በሕይወት መኖር ነው ።

በሐዋርያት ዘመን በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ ለአንድ ዓላማ በኅብረት ፣ በእኩልነት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መኖራቸውን ፣ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት አድርገው ለሁሉም እንደእየአስፈላጊነቱ ማከፋፈላቸውን ፣ ይኸውም ኅብረት ወይንም አንድነት በእምነት ፣ በተስፋ ፣ በፍቅር ላይ የተመሠረተ የፈቃድ እንጂ ግዴታ እንዳልነበረበት ፤ ይሁን እንጂ ግዴታ የለበትም ተብሎም በኅብረተሰቡ ላይ ሸፍጥንና ተንኮልን ማድረግ አለመቻሉን ፣ ለማድረግ የሞከሩ ቢኖሩም የሞት ቅጣት የተፈጸመባቸው መሆኑን ከታሪክ መረዳት ተችሏል ።

ቤተ ክርስቲያን ፣ ክርስቲያናት ፣ የእነርሱም አንድነት ፣ ቤተ ክርስቲያን ከተባለ ዓላማዋም በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም ይኸንኑ ማኅበረ ክርስቶስ መረዳትና ማገልገል ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መገኘት የሚችለው ኅብረተሰብእ ወይንም የሰው ልጆች አንድነት በአለበት በሚኖርበት ፤ በጸናበት ፤ በሚጸናበት መሆኑን ሲናገር "ሁለት ወይንም ሦስት በሰሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እገኛለሁ'' ይላል ። (ማቴ. 18 ቍ. 20)

ይህም አባባል የሚያስረዳን ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ለኅብረተሰብእ አገልግሎት መሆኑን ነው ።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ እንደገና የተወጠነው በክርስቶስ ሞት ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም የዚሁ ምስጢር ፈጻሚ ናት ።

ቤተ ክርስቲያን በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም የሰውን ዘር ሁሉ የምታገለግል የእግዚአብሔር መንግሥት ናት ።

ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኅዙናን ናት፡ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንን ከሕፃንነታቸው እስከ ዕረፍታቸው የምታገለግላቸው ፤ የምትረዳቸው ፤ የሕይወት ጉባዔ ናት ።

ቤተ ክርስቲያን ለሕያዋንና ለሙታን በየጊዜው ትጸልያለች ።

"ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው'' የሚለውን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ በተግባር ትፈጽማለች ።

ቤተ ክርስቲያን የተራቡትን ነፍሳት የምትመግብ ፣ የተጠሙትን አጠጥታ የምታረካ ፤ እንግዶችን ተቀብላ የምታስተናግድ ፤ የታረዙትን የምታለብስ ፤ የታመሙትን የምትጠይቅ ፤ የምታድን የታሠሩትን የምትጎበኝና እነዚህንም የመሳሰሉትን ሁሉ ለሰው ልጆች የምታደርግ ናት ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያንና ዓላማዋ ስንል ፣ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ከዚህ ዓለም ክፉ ነገር ሁሉ ርቃ እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል ነው ። በዓላማችንም እግዚአብሔርን ከማመስገንና ክብሩንም ከመናገር ፣ ሰውንም ከመርዳት የበለጠ ቅዱስ ተግባር የሌለ መሆኑን ከሰዎች ሕይወት መረዳት እንችላለን ።

ከዶ ግርማ ወ ቂርቆስ

# የምእመናን ድምጽ

በአንድ እግዚአብሔር አምነው በሥላሴ ስም ለተጠመቁ ሁሉ ምዕመናን የሚለው ስያሜ ይሰጣቸዋል ፤ ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያን አካላት በአንድ አቅጣጫ የሚገኙ ናቸው ምንም ሥልጣነ ክህነት እንዳላቸው ካህናት ውስጣዊውን አገልግሎት ከአፍአዊው አገልግሎት ጋር አዋህደው ለመሥራት ደረጃቸው ባይፈቅድላቸውም ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት ቤተ ክርስቲያንን የመርዳትና የማገልገል ግዴታ አለባቸው ።

በዕለተ እሑድ በእየሳምንቱና በልዩ ልዩ የበዓላት ቀኖች በቤተ ክርስቲያን እየተገኙያልተቆጠበመንፈሳዊአገልግሎትንለእግዚአብሔርየሚያቀርቡምዕመናንቁጥራቸውበቀላሉየሚገመትአይደለም።ምዕመናኑጾማቸውን ምጽዋታቸውንና ስዕለታቸውን ለፈጣሪያቸው ለማቅረብ የሚችሉ በቤተ ክርስቲያን መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ቤተ ክርስቲያን መማፀኛ ፤ መስገጃ ኃጢአትን ማስተሰሪያ ስለሆነች ምዕመናኑ ሁሉ ገጸ በረከታቸውን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ከመስጠት ይልቅ አውደ ምህረት በሆነችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሲያቀርቡ እጅግ በጣም ይደሰታሉ ።

ነገር ግን ምዕመናን በዓላትን አጿማትን ምክንያት በማድረግ ለጸሎትና ለስዕለት ፤ ለምጽዋትና ሌላም ልዩ ልዩ በጎ አድራጐቶችን ለመፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ የሚገጥሟቸው ችግሮች በርከት ያሉ መሆናቸውን ራሳቸው ይናገራሉ ፤ የሚደርሱባቸውንም ችግሮች ራሳቸው ለማስወገድ ባለመቻላቸው አንዳንዶቹ ለቤተ ክርስቲያን ኀላፊዎች ሲናገሩ ፤ ሌሎች ደግሞ እርስ በእርሳቸው በመነጋገር ብቻ የሚደርሱባቸውን ችግሮች ሁሉ ለማሳለፍ ይሞክራሉ ።

ምዕመናኑ ድምጻቸውን የሚያሰሙባቸው ችግሮች በርከት ያሉ ቢሆኑም ከችግሮቹ መካከል ጥቂቶቹን መጠቆም አስፈላጊ ይመስለኛል ።

በዓመት ፤ በዓል ፤ በወር በዓል ፤ በእየሳምንቱ እሁድ በቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን የሚቀርበው አገልግሎት የተሟላ አለመሆኑን አንዳንድ ምዕመናን ድምፃቸውን ዘለግ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ ። ከዚህም አልፈው በቤተ ክርስቲያን ያለው ስነ ሥርዓት በተቻለ መጠን እንዲሻሻል ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍልም ያመለከቱ ምዕመናንም ይገኛሉ ።

በእርግጥ የአገልግሎት ዋና መሠረቱ ሥነ ሥርዓት ነው ስነ ሥርዓት የጐደለው አገልግሎት ለምዕመናኑ የሚሰጠው ጥቅም አጥጋቢ ሊሆን አይችልም፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምዕመናን ድምጻቸውን ከሚያስተጋቡባቸው ችግሮች አንዱ የስብከት ሁኔታ ነው ፤ በዓመት በዓልም ሆነ በወር በዓል ትምህርት የሚሰጡት ሰባክያን የሚሰጡት ትምህርትምን ፍሬ ነገር እንዳዘለ ፤ በፊታቸው የተሰበሰበው ሕዝብ ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚፈለግ ሳያስቡ አፋቸው እንዳመጣ አገኘ አጣውን የቆጥየባጡን ቀበጣጥረው ሳንቲም ይጠይቃሉ በዚህ ጊዜ ምዕመናን ከጸሎታቸው ሳይሆኑ ወይም ከተሰጠው ስብከት ፍሬ ነገር ሳይቀስሙ እየተበሳጩና እያዘኑ ያለ ምንም ቁም ነገር ወደ ቤታቸው እንደሚመለሱ ራሳቸው ይናገራሉ ።

መላውን አድባራትና ገዳማት ወክለን ባንናገርም አንዳንዶቹ አድባራት አስተማሪ ሳያጡና ሳይቸግራቸው ሥነ ስርዓት ሳይጐድልባቸው አገልግሎታቸው በምዕመናን ዘንድ ተወዳጅነት ሳለው ፤ ከካህናቱ መካከል ፍቅርና





www.ethiopianorthodox.org

ሰላም ተለይተው አንድነት ፈጽሞ ጠፍቶ የፍቅር መዲና የሰላም መገኛ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ራሷ ከፍቅርና ከሰላም ተራቁታ አንድነትን አጥታ የጸብና የክርክር ፣ የጥላቻና የምቀኝነት መድረክ ሁና ስለምትገኝ ምዕመናኑ በሁኔታው እጅግ በጣም ማዘናቸውን ይናገራሉ ።

“ሰውን ከሰው ጋር የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው” እያሉ የሚያስተምሩ ካህናት እርስ በእርሳቸው ለመስማማት ባለመቻላቸው የተገላቢጦ ምዕመናኑ ካህናቱን በመምከርና በማስታረቅ ብዙ ጊዜ ያጠፋሉ ፤ ይህም በምዕመናን ላይ የሚያስደርሰው ቅሬታ የቱን ያህል መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም ። ሁለተኛው ችግር በአንዳንድ አድባራት ለምዕመናን የወንጌል ትምህርት አይሰጥም ምዕመናኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው አዳምጠውት የሚመለሱት ቢኖር መቅድም የከበሮ ድምፅ ነው ይባላል።እንዲሁም በታላላቅ አድባራትና ገዳማት ከተጠቀሱት ችግሮች ለየት ያለ ችግር አለ ።

አንዳንድ ምዕመናን ካህናት ለእኛ ለምዕመናን መንፈሳውያን መሪዎች ሲሆኑ ከእኛ የተሻሉ ሁነው አልተገኙም እንዲያውም የተንኮል ሥራ ሲሠሩ የሚታዩ እነርሱ ናቸው ፤ የሚሠሩትን ሥራ ስንመለከት እጅግ በጣም እናዝናለን እነርሱ የማይገባ ተግባር የሚሠሩ ከሆኑ ማንን አርአያ አድርገን ነው መልካም ሥራ ለመሥራት የምንችለው ? በማለት ሲበሳጩና ከቤተ ክርስቲያንም ለመራቅ ሲሞክሩ ይታያሉ ።

በጠቅላላው ካህናቱን መውቀስ አይገባም እንጅ አንዳንድ ካህናት ከመወቀስ አልፈው ሊከሰሱና ሊወቀሱ የሚያስፈልጋቸው ሁነው እናገኛቸዋለን የራሳቸውንም ሆነ የምዕመናንን ጥቅም የማያውቁና ያልተረዱ ካህናት ጥቂቶች አይደሉም ፤ ምዕመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን በማቅረብ ፈንታ የሚያርቁ ከእግዚአብሔር አንድነት የሚለዩበትን መንገድ የሚቀይሱ ካህናት መኖራቸው የሚካድ አይደለም ።

ሌላው የምዕመናን ችግር በሰበካ ጉባዔ አለመደራጀት ነው ለዚህ አለመደራጀታቸው እንቅፋት ሁነው የተገኙት የንስሐ አባቶች የሆኑ ካህናት መሆናቸውን በርከት ያሉ ምዕመናን ይናገራሉ ፤ በካህናት እንዳይፈረድባቸው ስለ ሰበካ ጉባዔ ጥናት አልተሰጣቸውም ስለዚህም የንስሐ ልጆቻቸው በሰበካ ጉባዔ የተደራጁ እንደሆነ ፀበል ሲረጩ ዝክር ሲባርኩ መስቀል ሲያሳልሙ ከምዕመናን የሚሰጣቸው አነስተኛ ገጸ በረከት ተከልክሎባቸው ጠማቸውን የሚያድሩ መስሎ ይታያቸዋል ።ከዚህም የተነሣ ልጆቻቸው በሰበካ ጉባዔ መዝገብ እንዳይመዘገቡ የሚታገሉ ቀሳውስት አሁንም ሀሳባቸውን እንዲለውጡ ምዕመናኑ አልሠሩም ፦ ለዚህ ጉዳይ መፍትሔው የሰበካ ጉባዔ ለካህናቱና ለምዕመናኑ ያለውን ዓላማ በቃልም ሆነ በጽሑፍ መልሶ መላልሶ ማስረዳት ይመስለናል ።

በተጨማሪ ከዚህ እጅግ ያልራቀ ፤ ምዕመናን ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ምክንያት አለ ፤ እያንዳንዱ ምዕመን የንስሐ አባት እንዲኖረው የቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ ያዝዛል ፤ በዚህም መሠረት ቀሳውስቱ በግልጽም ሆነ በስውር የንስሐ ልጆችን ይይዛሉ ፤ የንስሐ ልጆች ያሏቸውም ቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸውን የሚጠይቁባቸው ጊዜያቶች የታወቁ ናቸው ይኸውም ፤

ሀ- ዝክር ሲባርኩ
ለ - ፀበል ሲረጩ
ሐ - ክርስትና ሲያነሡ
መ - ሠርግ ሲያሠርጉ
ሠ - በዓመት በዓልና በመሳሰሉት ቀናት ብቻ ነው ።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በስተቀር በሌላ ጊዜ ለመምከርና ለማስተማር ወደ ንስሐ ልጆቻቸው የሚያደርጉት ጉብኝት የለም ሲያዝኑ ፤ ለማጽናናት ፤ ሲጣሉ ለማስታረቅ ሲበሳጩ ለማረጋጋት ፕሮግራም አውጥተው ምዕመናንን የማገልገል ፍላጐት ያላቸው ቀሳውስት ያሉ አይመስለኝም ቢኖሩም በቁጥር አነስተኛ ይሆናሉ ።

የንስሐ አባት መሆን ለመምከርና ለማስተማር ሲሆን ለስሙ ብቻ አባትነኝ ብሎ በትጋትና በንቃት ምዕመናንን ከልዩ ልዩ የኃጢአት ወጥመድ አለመጠበቅ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቅ መሆኑን ቀሳውስቱ መገንዘብ አለባቸው ።

አብዛኞቹ ቀሳውስት በቂ ዕውቀት ቢኖራቸውም እንኳን ለምዕመናን ትምህርት የመስጠት ፍላጐት የላቸውም ትምህርት ለምዕመናን እንዳበረከቱ አድርገው የሚቆጥሩት ቢኖሩ መስቀል ማሳለም ፀበል መርጨትንና ዝክር መባረክን ነው ።

ይህ ሁኔታ እስከ ዛሬ የነበረ ቢሆንም አሁንም ጨርሶ ያልተደመሰሰ በመሆኑ ቀሳውስቱ ይህንን ይዞታቸው ለውጠው በዘመናዊ ዘዴ መደርጀት ያለባቸው መሆኑንሊረዱት ይገባል፦ፀበል መርጨት መስቀል ማሳለም ዝክር መባረክ ኃጢአት አይደለም ስሕተቱ ከትምህርት ጋር አለመፈጸሙ ነው ።

አሁን ምዕመናን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አስተማሪዎችን በመጠየቅ ላይ ይገኛሉ ፤ የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ሳያናጉ የኦርቶዶክስ እምነትን ሳይለቁ ጊዜውን ተከትለው የሚያስተምሩ ምሁራን በብዛት መዘጋጀት አለባቸው ቀሳውስት ምዕመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን በትምህርት ማቅረብ በመልካም አርዓያነታቸው መሳብ ግዴታቸው ነው ።

ምዕመናን የቤተ ክርስቲያን ገንዘቦች ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያንም የምዕመናን ናትና ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠሩ ከቤተ ክርስቲያን ለመራቅ የሚፈልጉትን ምዕመናን በትምህርት የማሳመን ችሎታ ያላቸው ፤ ካህናት ተፈላጊዎች ናቸው ። ቀሳውስቱ ከምዕመናኑ የተሻለ አስተሳሰብ የሌላቸው የመንፈስ ደካማነት የሚታይባቸው ናቸው በማለት አንዳንድ ምዕመናን አስተያየታቸውን ይሰነዝራሉ ፤ ሌሎች ክፍሎች ደግሞ የካህናቱን እርስ በእርስ አለመግባባት እየተመለከቱ በአሁኑ ጊዜወደ ቤተ ክርስቲያን ከመቅረብ ይልቅ መራቁ የተሻለ ነው ይላሉ ።

ሆኖም ካህናቱ ዕውቀታቸውን የሚያሻሽሉበት መጥፎ ጠባያቸውን የሚያርሙበት በእየጊዜው ሴሚናር ስለሚዘጋጅ ምዕመናንን ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም ፤ ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን የማይገባ ሥራ ሲፈጸም ሲያዩ ለመራቅ ከማሰብ ይልቅ ድርጊቱን የመቃወምና የማስወገድ ሀላፊነት አለባቸው ቤተ ክርስቲያን የካህናት ብቻ ሳትሆን የእነርሱም ጭምር ናትና ።

በውጭ ሀገር የአብያተ ክርስቲያናት የገቢ ምንጮቻቸው ምዕመናን በመሆናቸው በስብከትና በትምህርት ከፍተኛ ስጦታ ያሏቸው ቀሳውስት እንደ ደመወዝ ጭማሪ ፤ እንደ ደረጃ ዕድገት ተደርጐ የሚሰጣቸው ስጦታ ቢኖር በቁጥር በርከት ያሉ ምዕመናን ወደ ሚገኝበት ደብር ተዛውረው እንዲያገለግሉ ማድረግ ነው ምዕመናን በርከት ካሉ በርከት ያለ ገቢ ስለሚገኝ ቀሳውስቱም በገቢው መጠን ደመወዛቸው ስለሚያድግላቸው ነው ።

ቀሳውስቱ በሚገባ የተማሩ በመሆናቸው በትምህርታቸው በአገልግሎታቸውና በስነ ሥርዓታቸው ምዕመናኑን ያስደስቷቸዋል ፤ ምእመናኑም ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱ የምትፈልገውን ገንዘብ ማንም ሳያስገድዳቸው አስበው በወቅቱ ይከፍላሉ ።ምዕመናኑም ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው ፍቅር ልባዊ በመሆኑ አልፈው ተርፈው በዓመት በዓል በእየሳምንቱእሁድ በርከት ያሉ ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያናቸው ያበረክታሉ ።

ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያናቸው የገንዘብ ችግር የለበትም ፤ ለተማሩ አገልጋዮቿ በቂ ደመወዝ ትከፍላለች ካራሷም አልፋ ተርፋ ሌሎችንም ሊቃውንት ለንባ ትምህርት እየጋበዘች ታስተምራለች ፤ እርዳታም ስትጠይቅ ከመስጠት እጅዋን አታጥፍም ።

የእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን መንግሥት አቀፍ ድርጅት እንጅ ምዕመናን አቀፍ ሁና ባለመቆየቷ የራሷን ካህናት በደመወዝ ለማስተዳደር በቂየሆነ የገንዘብ ኃይል አላገኘችም ድኩማንንም ለመርዳት አቅም የላትም ። ይኸውም ምዕመናኑ ቤተ ክርስቲያን ከእነርሱ የምትፈልገውን አስተዋጽኦ በወቅቱ ባለመክፈላቸው ነው እስከ ዛሬ ድረስ እንደሚታወቀው ምዕመናኑ ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ፤ ስለእነርሱ የተመሠረተች መሆኗን በሚገባ የተረዱት አይመስሉም ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ለዲያቆናት ለቀሳውስት ለመነኮሳትና ለጳጳሳት ብቻ የተመሠረተች ይመስላቸዋል ንዋያተ ቤተ ክርስቲያንንም ማሟላት ያለበት መንግሥት ያም ባይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሆኑ ጳጳሳት እየመሰሏቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቷት በገለልተኛነት እንጅ እንደራሳቸው አካል አድርገው አይደለም ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ምዕመናን የቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም የምዕመናን እንጅ የተለዩ ለተለዩ ሰዎች እንዳልተመሠረተች ተደጋግሞ ተገልጿል ። በእውነትም ናት ለተለዩ ሰዎች ለተለዩ ባለሥልጣናት የተመሠረተች ሳትሆን የተመሠረተችው ለማንኛውም ምዕመናን ነው ። በእምነታችን መሠረት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት ሊገኝ አይችልም ምዕመናን ድምጻቸውን ወደ እግዚአብሔር የሚያሰሙት በቤተ ክርስቲያን ነው ።

ምዕመናን በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያን የእነርሱ መሆኗን በመገንዘብ ላይ ስለሚገኙ ነውርና ነቀፌታ የሌለባቸው ራሳቸውን ለመግዛትና ለመቆጣጠር የሚችሉ አብዝተው ጠጥተው በመስከር ቤተ ክርስቲያንን የሚያሰድቡ የመምከርና የማስተማር ችሎታ ያላቸው መምህራን እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ በትክክለኛ መንገድ የሚራመዱ መልካም አርአያን የሚያሳዩ መምህራን ከተገኙ ቤተክርስቲያናችን የገንዘብም ሆነ የሰው ችግር አይኖርባትም ምዕመናንም ቢሆኑ በቤተ ክርስቲያን የሚፈለግባቸውን ድርሻ ከመክፈል ወደ ኋላ አይሉም ።

ምዕመናን ትናንት የጠየቁት ዛሬም የሚጠይቁት ሲያዝኑ የሚያጽናኗቸው ሲበሳጩ የሚያረጋጓቸው ፤ ሲቸገሩ የሚረዷቸው አስተማሪዎችን ነው በጠቅላላው ባይሆንም አንዳንድ ምዕመናን ቤተ ክርስቲያን ካህናት ማለታቸውን ትተው ቤተ ክርስቲያናችን ካህናቶቻችን ማለት ጀምረዋል ።

ካህናት የሚያገለግሉት ለራሳቸው እየመሰላቸው ከምንም የማይቆጥሯቸው ምዕመናን አሁን ካህናቱ የሚያገለግሉት ለእነርሱ ስለ እነርሱም ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን መሆኑን በመገንዘብ ለዕለት ምግባቸው ለዓመት ልብሳቸው የሚሆን ገንዘብ በማዋጣት ላይ መሆናቸውን ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ የምስራች ነው ይሁን እንጅ ምዕመናኑ መልሰው መላልሰው የሚጠይቁት አጥጋቢ ትምህርትን የሚሰጡ መምህራንን ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን የምዕመናንን ጥያቄ ማሟላት ኃላፊነት አለባት ።

ልሳኑ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org